# ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ፈራጅ?

## ለኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የተሰጠ ምላሽ



ከአያሌው ዋቀዮ

ጥር 2018

ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ፈራጅ ?

ቅጽ 1

2018 ዓ.ም

**ጸሓፊ_ አያሌው ዋቀዮ**

ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተም ሆነ የተወሰነን ክፍሎች በኢለክትሮን ማሽን ፥በፎቶ ኮፒ እና በድምጽ ማራባት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡ ፡ሆኖም ግን ለጥናት ለማስተማሪ እና በከፊል መረጃ መወሰድ ከተፈለገ የመጽሐፉ ስም የደራሲውን ስምና መጽሐፉ የተጻፈበትን ዓመተ ምህረት በመጥቀስ ለትርፍ ባልሆነ መልኩ ግልጋሎት ላይ ማዋል ይቻላል።

Authort_Ayalew Wakeyo

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form electronic, mechanical, photocopying, and recording.

Questions, comment, and criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to the author.

ጥያቄ፣አስተያየትም ሆነ ሒስ ካልዎት ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ያግኙን፡-

ኢ_ሜይል፡-ayalewwakeyo7@gmail.com

ስልክ 0953755701

# ማስታወሻነቱ

**በመንፈሳዊ ረገድ ላሳደጉኝ ለፓ/ር አለማየሁ ወ/ዮሐንስ እና ለወ/ዊት የሺህሐረግ መለሰ ማስታወሻ ትሁንልኝ !!!**

# ምስጋና

*በመጀመሪያ ይህ መጽሐፍ ተጽፎ እንዲጠናቀቅና ለእናንተ ለተወደዳችሁ አንባቢያን እንዲደርስ የረዳኝን፣ የጥበብና የእውቀት ሁሉ ምንጭ የሆነውን አሃዱ-ሥሉስ  አምላኬን ስም አከብራለሁ። ያለ እርሱ ረዳትነት ይህንን ከባድና ረቂቅ የሆነ የነገረ መለኮት ምስጢር መመርመርም ሆነ መጻፍ ባልተቻለኝ ነበር።በመቀጠልም፡-በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ወቅት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሃሳቦችና በነገረ መለኮት ትንታኔዎች ሃሳብ በመስጠት፣ በማረም እና በማበረታታት ከጎኔ ለነበሩ የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና ጓደኞቼ። መጽሐፉን በጸሎትና በምክር ለደገፉኝ ለቤተሰቦቼ። እንዲሁም ይህንን መጽሐፍ አንብባችሁ ገንቢ አስተያየታችሁን ለምትሰጡኝና እውነትን ለምትፈልጉ ቅን አንባቢያን ሁላችሁንም እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።*

## ማውጫ

መግቢያ ........ 6
የቃላት ትርጓሜ........ Error! Bookmark not defined.
1. የነቢይነት አገልግሎት........ 10
2. የክህነት አገልግሎት........ 12
3. የንጉሥነት አገልግሎት ........ 13
ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ? ........ 14
ሮሜ 8፥34........ 14
ዕብ 7÷25 ........ 17
አምላክነቱና አማላጅነቱ........ 19
ኢየሱስ በትስብዕነቱ ብቻ ሳይሆን በአምላክ-ሰውነቱ ነው ምልጃው ........ 21
ከትንሣኤ በፊትና ከትንሣኤ በኃላ የተደረገ ምልጃ ልዩነቱ........ 25
ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ከሆነ እንደት ፈራጅ ሆነ ? ........ 26
መካከለኛ ........ Error! Bookmark not defined.
ሊቀ ካህናት ........ 31
የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ክህነት........ 34
ጠበቃ........ 36
ከሞት በኃላ ምልጃ ወይም መማለድ የለም ........ 38
በፍጡራን ስም መማጸን አግባብነት አለውን? ........ 39
ጸሐይ የተጎጸፈች ሴት ማርያም ናት?........ 40
የጥንት ቤተክርስቲያን አበዎች ስለኢየሱስ አማላጅነት ምስክርነት ........ 40
መላእክትና ቅዱሳን መማለድ የማይችሉባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች........ 43
ጽዮን ድንግል ማርያም ናት ወይስ ሌላ? ........ 44
የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ብዙ ጊዜ የሚያነሱ ጥያቄዎች ........ 46
ማጠቃለያ (Conclusion) ........ 53
ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography) ........ 54

# መግቢያ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ወቅት ሆነ ካረገ በኋላ ብዙ የሐሰት አስተምህሮት ነበሩ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በሚመላለስ ጊዜ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር ልጅ ከአባቱ ዘንድ ይዘው የመጣውን እውነተኛ አስተምህሮት ላለመቀበል ስለ ወጋቸው ይከራከሩ ነበረ፤ እርሱ ካረገ በኋላም እውነተኛ ወንጌል የተቀበሉ ደቀመዛሙርቱ በብዙ ተጋድሎ ያልተበረዘ ወንጌል ለቀጣይ ትውልድ አስተላልፈው አልፈዋል። ከመጀመሪያው ምዕተ አመት ጀምሮ እስከ አሁኑ ክፍለ ዘመን ድረስ ብዙ የሐሰት አስተምህሮት ክፉኝ ቤተክርስቲያንን ብገዳደራትም የቤተክርስቲያን አባቶች በርዕቱ ሙትት አውግዘው ለቀጣይ ትውልድ የሚሆነውን ጽሑፎችን አበረክቶ አልፈዋል። አሁን ባለበት ወቅትም ሴሕት አስተምህሮት እንደ አሸን እየፈሉ ቢገኙም እንደ አባቶቻችን በቅን ልቦና በርዕቱ ሙትት ማውገዝ ይጠበቅብናል።

ይህንን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ያነሳኝ ዋና ምክንያት ወንጌል እየመሰከርኩ ባለ ወቅት አብዛኛው ጊዜ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት የሚጠየቀው ጥያቄዎች እንዲሁም በይነ-መረብ (በኢንተርኔት) ሠረገላ ላይ ተሳፍሬ ስዞር በድረገጽ ላይ አብዛኞቹ ኢየሱስ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም ብሎ ጽሑፍ በማግኘት እኔም እጄን ከማስታወሻዬ ጋር ለማስተም ወሰንኩ። እንዲሁም ብዙ አማኞች አማላጅ የሚለውን ትርጉም በተሳሳተ መንገድ ስተረጉሙና ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ፊት ቁጭ ብሎ አማላጅነትን እንደሚቀበል ስለሚመስላቸው ጭምር ነው። ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ፈራጅ የሚለው ይህ መጽሐፍ ኢየሱስ እንዴት እንደሚማልድ እና መቼ እንደሚፈርድ ባጭሩ የሚያስረዳ ሲሆን በተለይ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ብዙ ጊዜ የሚያነሱትን ጥያቄዎችን ጸሐፊው ይመልሳል። ኢየሱስ አምላክ ሆኖ እንዴት ይማልዳል፤ ፈራጅ ሆኖ እንዴት ይማልዳል፤ ፈራጅ ሆኖ እንዴት አማላጅ ይባላል፤ ወደ ማን ይማልዳል የሚሉትን ጥያቄዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተንተርሶ ጸሐፊው ይመልሳል። በመጨረሻ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሐሳብና የቃላት ድግግሞሽ ስታገኙ ሆን ተብለው የተደረጉና አስፈላጊ መሆናቸውን እንድትረዱልኝ እወዳለሁ። ለስልጠና ሆነ ለተለያዩ ዓላማዎች ለመገልገል ከተፈለገ መጽሐፍና ገጹ እንዲሁም ጸሐፊው በግርጌ ማመልከት ይገባል።

# የቃላት ትርጓሜ

በቅድሚያ፡- ማለደ፣ አማለደ፣ አማላጅ፣ ማላጅ፣ ተማላጅ፣ የሚማላድ፣ ምልጃ፣ ጠበቃ እና አስታራቂ የሚሉትን የቃላት ትርጉም እንመልከት።

**ማለደ**፡- የሚለው ቃል ሁለት ዓይነት ትርጉም ሲኖረው የመጀመሪያው ማለደ ማለት በማለዳ ወይም በጥዋት ተነሳ ማለት ነው። ለምሳሌ፡-

*የመንግሥተ ሰማያት ለወይን አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስላለችና ማቴ 20፥1 ሕዝቡም ሁሉ ይሰሙት ዘንድ ማልደው በመቅደስ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡ ሉቃ 21፥38 አቢሜሌክም በነጋታው ማልዶ ባሮቹን ሁሉ ጠራ ዘፍ 20፥8 ፲ሳሙኤልም በነጋው ሳኦልን ለመገናኘት ማለደ ፲ኛሳሙ 15፥12 ቃልህን አስብ ዘንድ ዓይኖቼ ለመማለድ ቀደሙ መዝ 119፥148*

ማለደ፣ ማለደው፣ ማለዱ፣ ለመማለድ ቃላት የሚያመለክቱት የቀደሙ ሳይሆን መነሳት ማለት ነው እንጂ ፈጣሪውን መለመን በጸሎት ለማመልከት አይደለም። ይህ መነሻ ሲሆን ትርጉሙም ለመነ፣ ተማጸነ፣ ለመማለድ ተነሳ ማለት ነው። አንድ ሰው ስለ ራሱ ወይም ስለ ሌላ ሰው ጉዳይ ለአንድ የበላይ አካል ወይም ለባለስልጣን ጥያቄ ሲያቀርብ ማለደ ይባላል፡፡

**ማለደ**፡- ለሚለው ቃል ሁለተኛው ትርጉም ለመነ፣ ደጅ ጠና የሚል ትርጉም አለው። ለምሳሌ በሥጋ ወራት ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ለምኗል ሉቃ 22፡32፤ የእስራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር አልታዘዝም ስሉ ለእርሱ አልታዘዝ ያሉትን አጥፍቶ አዲስ ትውልድ ለሙሴ ለመስጠት ሲያስብ ሙሴ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳያጠፋ ማልዷል ዘኁ 14፡19 አብርሃም ለሰዶም ማልዷል፡፡ ዘፍ 19፥16-33

**አማለደ**፡- የሚለው ቃል በግእዝ ግስ ተበለ ማለት ሲሆን ይህም በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ወገኖች መካከል የተፈጠረውን ቅሬታና ጥል እንዲወገድ ማድረግ ወይም አስታረቀ ማለት ነው። የሚያማልደው ሰው ለለማኙ ይቅርታ እንዲያደርጉለትና በመካከላቸው ሰላም እንዲወርድ በሰዎች ስም ተማጸነ ማለት ነው ወይም በሁለት ወገኖች መካከል ገብቶ አስታረቀ፣ ስለ ሌላው ሰው ይቅርታን ወይም ምህረትን ለመነ ማለት ነው። ለምሳሌ፡-እገሌ ለጓደኛው አማለደለት ሲባል፣ ጓደኛው ካለበት ችግር ወይም ቅጣት እንዲያመልጥ በመካከላቸው ገብቶ ለመነለት ማለት ነው።

**አማላጅ**፡- ማለት አንድ ሰው በራሱ ማድረግ የማይችለውን አቅም የሚያስረክብ አማላጅ ይባላል። አንዱ ለሌላው ይቅርታን፣ እርቅንና ሰላምን ለማስገኘት በአድራጊውና በተቀባዩ መካከል የሚያገናኝ መስመር ነው። ተግባሩን የሚያከናውነው ሰው ወይም አካል ነው። በሁለት ወገኖች መካከል በመቆም አንደኛው ወገን ለሌላኛው ይቅርታ እንዲያደርግለት የሚጠይቅ፣ የሚማጸን ወይም የሚለምን ማለት ነው። ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ አማላጅ ነበር እንዲሁም ሊቀ ካህናትም አማላጅ ነበሩ።

**ማላጅ፡-** ይህ ቃል "ማለደ" ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን፣ የሚለምን፣ የሚማጸን ወይም ልመና የሚያቀርብ ማለት ነው። ብዙ ጊዜ "አማላጅ" ከሚለው ቃል ጋር በተመሳሳይ ፍቺ ያገለግላል።ሁለት ሰዎች እንዳይጣሉና አንድ ሰው ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚለምን ማላጅ ይባላል።

**ማስታረቅ**፡- የሚለው ቃል "katallasso" ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም "kata/ከታ" እና "allosso/አሎሶ" ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገኘ ነው። ትርጉሙ በሁለት ወገኖች መካከል ወዳጅነትን ማስፈንና ማስማማት የሚል ትርጉም አለው። በተጣሉ ወይም በተጋጩ ሁለት ወገኖች መካከል ገብቶ ሰላምን የሚፈጥር፣ ቂምን የሚያስወግድ ማለት ነው። አስታራቂ ትኩረቱ ጥፋተኛን መፈለግ ሳይሆን፣ በሁለቱም ወገኖች መካከል እርቅና ስምምነት እንዲወርድ ማድረግ ነው።

**ምልጃ**፡-ራሱ የልመናው ሂደት ወይም ተግባሩ ነው። ስለ አንድ ሰው የሚቀርብ መማጸኛ፣ ልመና ወይም በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ የማስታረቅ ስራ "ምልጃ" ይባላል። በተጨማሪ የመለመን አገልግሎት ማለት ነው። የምልጃ መለመን ብቻ ሳይሆን የማስታረቅም አገልግሎት ነው። ማስታረቅና መለመን የቃል ፍቺቸው ቢለያይም ዓላማቸው ግን ተመሳሳይ ነው። ይህም የራቁ እንዲቀርቡና የተጣሉ እንዲታረቁ የሚያደርግ አገልግሎት ነው (2ቆሮ 5፥18-20፣ ኤፌ 6፥18-19)። መጽሐፍ ቅዱስ ለሌሎች እንድንጸልይ (እንድንማልድ) ያዝዛል። ስለ ሌሎች መጸለይ ወይም መማለድ ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ ኃላፊነትና አገልግሎት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለሌሎች የጸለዩ (የማለዱ) ሰዎች አብርሃም (ዘፍ 18፥1-33)፣ ዳዊት (መዝ 72፥1-20)፣ የኢየሱስ እናት ማርያም (ሉቃ 1፥46-55)፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (ሮሜ 10፥1፣ 1ጢሞ 2፥1-7) ወዘተ ናቸው። በምድር ላይ ሌላ ለሌላ መስበክም ማስተማርም መጸለይም ሆነ መምከር ይቻላል። ግን ይህ መስበክ፣ ማስተማር፣ መጸለይ ወይም መምከር ገደብ አለው። ገደቡም በሥጋ ሞቶ ወደ አምላክ እስከሄደ ነው። ይህም በሥጋ ማለትም በምድር ላይ እያለ ብቻ ነው። ከሞት በኋላ መጸለይ ሆነ መስበክ የለም። ይልቁንም ዕለት ዕለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ማምለክ እንጂ። በአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ጸልዩ ተጽዕኖ ማምጣት ይቻላል፤ ነገር ግን በሰማያዊ (በትንሣኤ) አካል ሆኖ በሞቱ ሰዎች ላይ ምንም ተጽዕኖ አያመጡም። ይህ ማለት በቅዱሳን ምልጃ አማካኝነት ነፍስን ከሲኦል ወደ መንግሥተ ሰማያት፤ ከመንግሥተ ሰማያት ወደ ሲኦል ማስገባት ሆነ ማስወጣት ለማንም አልተሰጠም። ይህን ሥልጣን ያለው የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ ያለው የይሁዳ አንበሳ የናዝሬቱ ኢየሱስ ብቻ ነው። እንዲህ ስንል ግን ኢየሱስ ወደ ሲኦል የገቡትን ያድናቸዋል ማለት ሳይሆን በሞትና በሕይወት ላይ ሥልጣን እንዳለው ለማሳየት ያህል ነው። (ዕብ 9፥27)

**መማለድ፡-** የሚለው ማለደ ከሚለው ስርወ ቃል የተገኘ ሲሆን በማለዳ ገብቶ ፍርዳቸውን ነፃ ለማውጣት ከሚደረግ ጥረትና ይግባኝ ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው። ይህም ደግሞ እኛን ወክሎ በአብ ፊት መታየትን ይግባኝ ማቅረብን ያመለክታል ብለን እንረዳለን።

**ተማላጅ (የሚማለደው)፡-** ይቅርታ እንዲያደርግና እንዲታረቅ የሚለመን ሰው ተማላጅ ወይም የሚማለድ ይባላል። ልመናው ወይም ምልጃው የሚቀርብለት ባለቤት ነው። ማለትም ምህረትን፣ ይቅርታን ወይም ፈቃድን እንዲሰጥ የሚለመነው አካል "ተማላጅ" ይባላል። ምልጃውን ተቀብሎ ይቅር የሚል ወገን ነው።

**<u>ማለደ (አማለደ)፡-</u>** ማለደ የሚል ቃል ከላይ እንደየነው መማለድ ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም ስለ ሌላ ሰው ወይም ስለ ሦስተኛ ሰው ለመነ ወይም ተማጸነ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ፍርድ ቤት ቢቀርብ የተከሳሽ ጠበቃ ስለ እርሱ ዳኛውን ሊያማርን ወይም ሊያማልድ ይችላል። ማለትም ዳኛው እንዳይፈርድበት ወይም ቅጣቱን እንዲቀልለት ሊለምንለት ይችላል ማለት ነው።

**ጠበቃ፡-** በህግ ወይም በማህበራዊ ጉዳይ ለአንድ ሰው መብት የሚቆም፣ የሚከራከር ወይም ጥበቃ የሚያደርግ ማለት ነው። ጠበቃ የአንድን ሰው ጥፋተኝነት ወይም ንጽህና በህግ ፊት ይሞግታል፤ እንዲሁም በችግር ጊዜ ደጋፊ ሆኖ የሚቆም አካል ነው።

---

[1] *ማለደ(interpose)awoke.in.the.early.hours.of.the.morning ማለደ(Intervene,get.up.before.daylight,get.up.early)አማለደ(reconcile,interceded) ተማለደ(was.petitioned,was.pleaded)ማለዳ(early.morning,dawn).አማላጅ (intercession)ምልጃ(intercect)*[2] *Reconciliation.means.to.interpose,to.intervene,.and.create relationship or friendship* [3] *የአማላጅ ተግባር ምልጃ ይባላል ፡፡*

ማለደ የሚለው ቃል ኢየሱስን በተመለከተ ያለውን ትርጉም አብረን እንቃኝ፡፡በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ቆሞ ማገናኘት የሚችሉ የታወቁ.ሦስት ዓይነት አገልግሎቶች አሉ እነርሱም፡-

ሦስት ዓይነት አገልግሎቶች

1. የነቢይነት አገልግሎት

2. የክህነት አገልግሎት

3. የንጉሥነት አገሎግሎት

ስለ ኢየሱስ አማላጅነት ለመረዳት እንድንችል ከላይ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶችን ትርጉማቸውን እንመለከት፡-

## 1. የነቢይነት አገልግሎት

በዕብራይስጥ ናቢ (Nabi[3]):የሚለው ቃል "መፍለቅ" ወይም "መዝለል" ከሚል ስር የመጣ ሲሆን፣ ትርጉሙም "የተቀበሉትን መለኮታዊ መልዕክት እንደ ውሃ ምንጭ የሚያፈልቁ"ማለት ነው። ነቢይ ከራሱ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የፈሰሰለትን ቃል ለሰዎች የሚያፈስ አካል ነው።

በግሪክ "ፕሮፌቴስ" (Prophetes):"ፕሮ" (በፊት/ስለ...) እና "ፌሚ" (መናገር) ከሚሉ ቃላት የተዋቀረ ነው። ትርጉሙም "ስለ ሌላው የሚናገር" ወይም "አስቀድሞ የሚናገር" ማለት ነው። ይህም ነቢዩ የእግዚአብሔር አፈ-ቀላጤ መሆኑን ያረጋግጣል። የነቢይነት አገልግሎት አጀማመር በታሪክ ውስጥ በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች አሉት፡- ጥንታዊው አጀማመር (ከሙሴ በፊት) ገና በሰው ልጅ ታሪክ መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር ለሰዎች ይናገር ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ "ነቢይ" ተብሎ የተጠራው አብርሃም ነው (ዘፍጥረት 20፥7)። በዚህ ዘመን ነቢይነቱ ከቤተሰብ አባትነት (Patriarchal) ጋር የተያያዘ ነበር። ሁለተኛ ደረጃ የነቢይነት አገልግሎት መመስረት (የሙሴ ዘመን) የነቢይነት አገልግሎት እንደ አንድ ተቋም ወይም ሥርዓት የተጀመረው በሙሴ ዘመን ነው። ሙሴ "የነቢያት ሁሉ አለቃ" ተብሎ ይታወቃል።እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቀጥታ ሲናገር ሕዝቡ ስለፈሩ፣ "እግዚአብሔር ለአንተ ይናገር፣ አንተ ደግሞ ለእኛ ንገረን" ብለው ሙሴን መካከለኛ አደረጉ (ዘጸአት 20፥19)። እግዚአብሔርም ይህንን ወዶ "እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ" በማለት የነቢይነት አገልግሎት በመካከለኛነት እንዲቀጥል አደረገ። በመሳፍንት ዘመን የእግዚአብሔር ቃል "ውድ" (ብርቅ) ሆኖ ነበር። ነገር ግን ነቢዩ ሳሙኤል የነቢያትን ማኅበር ወይም "የነቢያት ትምህርት ቤት" በማቋቋም አገልግሎቱ በስፋትና በሥርዓት እንዲቀጥል አድርጓል (1 ሳሙ 10፥5)። የነቢይነት ዋና ተግባራት (ምንነቱ) ነቢይ ሲባል ስለ ወደፊቱ የሚናገር (Foretelling) ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አሁን ላለው ትውልድ የሚያስተጋባ (Forthtelling) ነው። ሦስት ዋና ዋና ተግባራት አሉት፡-

**የእግዚአብሔር አፍ መሆን** ማለትም እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ ላይ ቃሉን ያኖራል። "እነሆ ቃሌን በአፍህ አኑሬአለሁ" (ኤር 1፥9)።

**ነቢያት መካከለኛ ናቸው** ከእግዚአብሔር ወደ ሕዝብ መልዕክት ያመጣሉ፤ ከሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ደግሞ ስለ ሕዝቡ ይማልዳሉ (ይጸልያሉ)።

**የኪዳን ጠባቅ ናቸው** ሕዝቡ ከእግዚአብሔር ሕግና ቃል ሲወጡ ተግስጽና ንስሐን በማምጣት ወደ ኪዳኑ ይመልሳቸዋል።በብሉይ ኪዳን የነበሩ ነቢያት ሁሉ "ጥላ" ነበሩ። እውነተኛውና ፍጹሙ "ናቢ" (አፈ-ቀላጤ) ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሌሎች ነቢያት "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" ሲሉ፣ እርሱ ግን "እኔ እላችኋለሁ" በማለት የቃሉ ባለቤት መሆኑን አሳይቷል። እርሱ የእግዚአብሔር "ቃል" (Logos) በመሆኑ፣ የነቢይነት አገልግሎት በእርሱ ዘንድ ፍጻሜውን አግኝቷል። ነቢይነት የተጀመረው እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማደስ ካለው ፍላጎት የተነሳ ነው። የቃሉ አጀማመርና ስርወ-ትርጉም የሚያሳየን ነቢይነት የሰው ጥበብ ሳይሆን መለኮታዊ "ፍሳሽ" መሆኑን ነው።

---

3^nâbiy' [H503] /Naw_beê means inspired man

Grk [4] kôhên/ko-hane' [H3548] primitive root, apparently meaning to mediate in religious services

## 2. የክህነት አገልግሎት

"ካህን" የሚለው ቃል kôhên (ኮሄኔ)ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተገኘ ነው።ትርጉሙም የሃይማኖት ሥርዓትን በመካከለኛነት የሚፈጽም አካል ማለት ነው።ዋና ተግባሩም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኝ መካከለኛ ሆኖ ማገልገል ነው። የክህነት አገልግሎት አጀማመር (ታሪካዊ እድገት) ስንመለከት የክህነት አገልግሎት በሦስት ዋና ዋና የእድገት ደረጃዎች አልፏል፡-

**የግል መስዋዕት (የመጀመሪያው ደረጃ)፡-በጥንት** ዘመን እንደ ቃየልና አቤል ያለ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መስዋዕት ያቀርብ ነበር (ዘፍ 4፥3-4)።

**የቤተሰብ ክህነት (ሁለተኛው ደረጃ)፡-** በኋላም እንደ ኖኅና አብርሃም ያሉ አባቶች ለቤተሰቦቻቸው መስዋዕትን ይሰዉ ነበር (ዘፍ 8፥20፤ 12፥7)።

**የተደራጀ ክህነት (የሕግ ዘመን**)፡-ሕግ ሲሰጥ አሮንና ልጆቹ ለእስራኤል ካህናት እንዲሆኑ ተመረጡ (ዘጸ 28፥1)። ከእነርሱ ውጭ ያሉት ሌዋውያን በመቅደስ ያገለግሉ ነበር እንጂ መስዋዕት አያቀርቡም ነበር (ዘኍ 3፥5-10)።

አልፎ አልፎ እግዚአብሔር ራሱን ለገለጠላቸው እንደ ጌዴዎን፣ ኤልያስና ኢዮብ ያሉ ሰዎች መስዋዕትን ይሰው ነበር (መሳ 6፥18-26፤ 1ነገ 18፥30፤ ኢዮ 1፥5-10)።

የክህነት አገልግሎት ከምልጃ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው፡-የካህናት ዋና አገልግሎት በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ማገልገል በመሆኑ፣ ሕዝቡን ወክለው ወደ እግዚአብሔር ይቀርባሉ።ካህኑ የሕዝቡን ኃጢአት ይዞ መስዋዕት በማቅረብ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል፤ ይህም የተግባር ምልጃ ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎት ፍጹም ባለመሆኑ፣ አገልግሎታቸው ፍጹም በሆነው በኢየሱስ ተተክቷል። ኢየሱስ ፍጹም ካህን እንደመሆኑ መጠን፣ በራሱ መስዋዕትነት ሰውንና እግዚአብሔርን ለዘላለም የሚያገናኝ ፍጹም አማላጅ ሆኗል።

## 3. የንጉሥነት አገልግሎት

በመጽሐፍ ቅዱስ "ንጉሥ" (በዕብራይስጥ Melek፣ በግሪክ Basileus) ማለት ገዥ፣ መሪ፣ ጠባቂና ዳኛ ማለት ነው። የንጉሥነት አገልግሎት ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

መግዛትና ማስተዳደር( በሥልጣን ክልሉ ውስጥ ሥርዓትን ማስፈን)፣መጠበቅ፡-(ሕዝቡን ከጠላት መከላከልና ደኅንነታቸውን ማረጋገጥ) እና መፍረድ(እውነትን ከሐሰት መለየትና ፍትሕን በምድር ላይ ማንገሥ)

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን "የነገሥታት ንጉሥ" ይለዋል። ማንኛውም ምድራዊ የንጉሥነት አገልግሎት ምንጩ እግዚአብሔር ነው። መዝሙር 47፡7፡- "እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና።" እግዚአብሔር ንጉሥ ነው ሲባል ፍጥረታትን በሙሉ በቃሉ የሚገዛ፣ ለሁሉም የሚያስፈልገውን የሚሰጥና የጽድቅ ፍርድን የሚፈርድ መሆኑን ያሳያል። በአዲስ ኪዳን የንጉሥነት አገልግሎት ፍጹም ሆኖ የተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የክርስቶስ ንጉሥነት ከምድራዊ ነገሥታት የሚለየው በሚከተሉት መንገዶች ነው፡-

ዘላለማዊነት፡- መንግሥቱ የማያልፍና ዘላለማዊ ነው። (ሉቃስ 1፡33)

መንፈሳዊነት፡- "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም" (ዮሐንስ 18፡36)

ድል አድራጊነት፡- በሞትና በሰይጣን ላይ በመንገሥ የሰው ልጅን ከባርነት ነፃ አውጥቷል።

የንጉሥነት አገልግሎት መገለጫዎች የመጀመሪያ እረኝነት ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ንጉሥነት ከእረኝነት ጋር የተያያዘ ነው፤ንጉሥ ሕዝቡን እንደ እረኛ ይመራል፣ ይመግባል፣ ይጠብቃልም። (መዝሙር 78፡70-72) አገልጋ፡- የክርስቶስ ንጉሥነት "ለማገልገል እንጂ እንዲያገለግሉት" የመጣ ንጉሥነት ነው። ስለዚህ እውነተኛ የንጉሥነት አገልግሎት በትሕትና ሌሎችን ማገልገል ነው።የንጉሥነት አገልግሎት ማለት ሥልጣንን ለራስ ክብር መጠቀም ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ቃል እየተመሩ በኃጢአትና በጨለማ ላይ በመንገሥ፣ ጽድቅና ሰላም በሰው ልብና በዓለም ላይ እንዲሰፍን የማድረግ መንፈሳዊ ተልእኮ ነው። 1ዮሐ 2-1

ጠቀለል ስናደርገው ነቢይ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለሕዝቡ የሚያስታውቅ ስሆን ፥ካህን ደግሞ ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ፡ጸሎትንና ምስጋናን ያቀርባል ፤ንጉሥ ደግሞ የእግዚአብሔር ወክል በመሆን ሕዝቡን ያስተዳድራል፡፡ ሦስቱም ተጠርነታቸው ለእግዚአብሔር ሆኖ ነቢያት እግዚአብሔርን ወክሎ ለሕዝቡ ይናገራሉ ፥በዚህም የእግዝአብሔር አፍ ይሰኛሉ፡፡ካህን ደግሞ ሕዝቡን ወክሎ ለእግዝአብሔር ይናገራል በዚህም የሕዝቡ አፍ ይሰኛል ፡፡ ኢየሱስ እነዚህን አገልግሎት ሁሉ አገልግሏል፡እንደ ነቢይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አስታውቋል ፥እንደ ካህን ለኃጢአታችን ራሱን መሥዋዕት አድርጎ አቅርቧል፥እንደ ንጉሥ ደግሞ አጽናፈ አለምን ይገዛል፥ ቤተክርስትያንን ያስተዳድራል፡፡

## ኢየሱስ አማላጅ ወይስ ተማላጅ?

ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ (የሚማልደው) ወይም ተማላጅ (የሚማለድለት) የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ብዙዎች ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ስለሆነ ተማላጅ እንጂ አማላጅ አይደለም ሲሉ ይመልሳሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዚህ ነገር ምን ይላል ብለን መጠየቅ ብልህነት ነው። እስኪ ከቃል እግዚአብሔር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት አብረን እንቃኝ፡- በብሉይ ኪዳን ዘመን የሊቀካህናት የመጀመሪያው ሥራ የማማለድ ሥራ ነው፤ እንዲሁም ኢየሱስ ሊቀካህን ስለሆነ የመጀመሪያው ሥራ የምልጃ ሥራ ነው። የሐዲስ ኪዳን ሊቀካህን የሆነው ኢየሱስ የሠራቸው ሥራዎች ለኃጢአታችን ፍጹም የሆነ መሥዋዕት ራሱን አቅርቧል። ዕብ 4፥14፤ 9፥24፤ 10፥4 ዘወትር በእግዚአብሔር ፊት ይታይልናል፤ ዕብ 9፥7፤ 6፥19-20፤ 10፥19-22 ዘወትር ስለ እኛ ይማልዳል። ሮሜ 8፥34፤ ዕብ 7፥25።

እስከ አሁን ደግሞ ክፍሉን በየአንዳንዱ ቋንቋ ወደ መመርመር እንለፍ።

## ሮሜ 8፥34

***Τίς ὁ κατακρινῶν; Χριστὸς Ἰησοῦς ὁ ἀποθανών, μᾶλλον δὲ ἐγερθείς ἐκ νεκρῶν, ὅς ἐστιν ἐν δεξιᾷ τοῦ θεοῦ, ὃς καὶ ἐντυγχάνει ὑπὲρ ἡμῶν.***

***"who is he that condemneth? It is Christ that died, yea rather, that is risen again, who is even at the right hand of God, who also maketh intercession for us" KJV holy bible***

የሞተ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለውና ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በ 1962 የታተመ መቅ ላይ

« ማነው የሚፈርድ ? ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርድባቸዋል? እርሱ ስለእኛ የሞተ ፥ ከሞት ተነስቶ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ ፥ ስለእኛ የሚማልድ ነው» በ 1997 በታተመው እ.መ.ት ላይ

ከላይ በተለያዩ ቋንቋ ለማየት እንደሞከርነው ክፍሉን ደግሞ ወደ መመርመር እንለፍ፤ ታዲያ ለዚህ ምን እንላለን ? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ፥ ማን ሊቃወመን ይችላል? ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት ፤ ነገር ግን ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ ፤ ሁሉንስ ነገር ከእርሱ ጋር እንደምን በልግስና አይሰጠንም ? እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማነው ? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው ታዲያ የሚፈርድ ማነው ? የሞተው ፤ እንዲሁም ከሞት የተነሣ ፤ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ ይማልዳል ። ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማነው ?

እንግዲህ ለሰዋሰዋው አወቃቀሩን ስንመለከት ሮሜ 8:31-39 ክፍል የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ በኩል ለእኛ እንዴት እንደተገለጠ ያሳያል ። ይህም ጳውሎስ ማንም በእኛ ላይ መፍረድ እንደማይችል አምስት ጥያቄዎችን እያነሳ ያስረዳል።

1. እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል ?

“ማን” የሚለው ተውላጠ ስም የሚያመለክተውም በስሙ ያልተጠቀሰውን ሰይጣንን ነው። ይህም አንቀጽ ከቁ 31-39 የብሉይ ኪዳን የነቢያትን የአጻጻፍ ስልት ነው፤ ማለትም የፍርድ ቤት ጉዳይ ያሳያል  የፍርድ ቃላት የሆኑት :-

- ተቃውሞ ቁ 31
- ክስ ቁ 33
- ከወንጀል ነጻ ቁ 33
- ጥፋተኝነት ቁ 34 እና
- መማለድ ቁ 34

እነዚህ ሰይጣን ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ሆኖ ቀርቧል ፤ በተቃራኒ ደግሞ ኢየሱስ ተከላካይ ጠበቃ ሆኖ ቀርቧል ። በምስሉ ላይ የሚገኘው ጽሑፍ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

2. እግዚአብሔር ለገዛ ልጁ ሳይራራ ስለ እኛ አሳልፎ ከሰጠው እንዴት ከልጁ ጋር ሁሉን ነገር በነጻ አይሰጠንም?

3. እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው

4. ማነው የሚፈርደው? ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርድባቸዋል? እርሱ ስለ እኛ የሞተ ከሞት ተነስቶ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠ ስለ እኛም የሚማልድ ነው። ከላይ እንዳየነው ሰይጣን ከሳሽ ሲሆን፤ ኢየሱስ ደግሞ ጠበቃ ሆኖ ቀርቧል። በዚህ ክፍል በክርስቶስ ደም በተዋጁት በእግዚአብሔር ምርጦች ላይ ማንም ሊፈርድ እንደማይችል ሦስት ምክንያቶች ቀርበዋል፤ እነርሱም፡-

1. ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷል ቁ 34
2. በአባ ቀኝ ሆኖ፤ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ኖሯል
3. ስለ እኛ ይማልዳል ቁ 34

ክፍሉ ኢየሱስ አማላጅ መሆኑን ያመለክታል። አንቀጹን ልብ ብለን ካየነው የሞተ፣ ከሙታን የተነሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው የሚለው ሐረጎች ስናይ፤ የሞተና የተነሣ የሚሉት በኃላፊ ግሥ (past tense) የተቀመጡ ሲሆኑ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው የሚለው ግን በአሁን ግሥ (present tense) ተቀምጧል። ከረገ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ዕርፍ (ቀኝ) አለ። ማር 16:19 ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ካለ በኋላ **ስለ እኛ የሚማልደው መሆኑን ያመለክታል።

አንዳንድ የሀገራችን ሰዎች በግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ወይትዋቀስ በአንቲአነ የሚለውን ስለ እኛ የሚፈርድ ብሎ በመተርጎም ቃሉን ሲያጣምሙ ይታያሉ። ይትዋቀስ የሚለው ተዋቀሰ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ተከራከረ፣ ተሟገተ ማለት እንጂ ፈረደ የሚል ትርጉም የለውም። ተዋቀሰ ማለት መከራከር ወይም መሟገት ማለት ሲሆን ይትዋቀስ በአንቲአነ ማለት ደግሞ ስለ እኛ ይከራከራል፣ ይሟገታል ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ግዕዝና ግሪኩን ቋንቋ መሠረት ያላደረገ ስለ እኛ የሚፈርደው ብለው ተርጉመዋል። ይህም ኢየሱስ አማላጅ ከሆነ የቅዱሳንና መላእክት አማላጅነታቸው ስለሚቀርባቸው በመስጋት ነው። የልጅ የፍጡራን ባሕርይ እንጂ የአምላክ ባሕርይ አይደለም ብለው ከውሸት በመነጨ ፍርሃት አላቸው። እውነት ሰለዚህ ነገር ይናገራል ወይ ካልን በጭራሽ የሚል ነው። ሮሜ 8:33 እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው። የሚኮንንስ ማን ነው? መልሱ ማንም

።እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማንም አይቃወመንም፤ እግዚአብሔር ከመረጠን ማንም አይከስንም፤ እግዚአብሔር ካጸደቀ ማንም አይኮንንም የሚል ነው መልእክቱ። በከፍሉ አከባቢ ይኮንናል፣ ይፈርዳል የሚለው ኃይለ-ቃል በአንቀጹ ላይ የለም። ጥቅሱ ኢየሱስ ፈራጅ ነው አይልም ይልቁንም ማነው የሚፈርድ? ኢየሱስ ክርስቶስ ይፈርድባቸዋል? እርሱ የሞተ፣ ከሞት ተነሥቶ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ የተቀመጠ፣ ስለ እኛ የሚማልድ ነው የሚለው። መላእክት ሆነ ድንግል ማርያም አማላጅ እንድሆኑላቸው የሚጋቱ ሰዎች በድሮ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚፈርድ ነው ይላል ብለው ይደመድማሉ። እሱም የፕሮቴስታንት መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ ነው አማላጅ የሚለው። እነርሱ እንደተባሉ ቃሉ ግን ከዚህ የራቀ ነው፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ሲጻፍ በግሪክ እንቱክሃኑዬ (en-toong-khan'-o) የሚማልድ ማለት እንጂ ካታክሪኖ (katakrino) የሚፈርድ በማለት አላስቀመጠም ነበር። በግሪኩ ደ ማለት ደግሞ Moreover የሚል ላይ መስተዋቅር በመጠቀም ከእግዚአብሔር በተሰጠ መልኩ ስለ ኢየሱስ ማንነትና አማላጅነት ይናገራል። የሚማልደው የሚለውን የሚፈርድ እያሉ የሚያስቀምጡት እሳቤያቸውን ጽኑ ለማድረግ መሞከር ነው። በመሠረቱ ጴንጤ የሚባል እስከ አሁን የታተመ መጽሐፍ ቅዱስ የለም። ይልቁንም ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ያሳተመችውንና በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ማለትም ኦርቶዶክስ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት በጋራ ሆኖ ያሳተሙትን ነው። እየተጠቀሙ ያሉት ክፍሉ በግልጽ ኢየሱስ አማላጅ ነው እንጂ ፈራጅ ወይም ተማላጅ አይደለም ይላል። ስናጠቃልል ያማልዳል" ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል "entynchanō" (ἐντυγχάνω) ነው። ይህ ቃል ለአንድ ጉዳይ ወደ ባለሥልጣን ወይም ወደ ንጉሥ መቅረብን ያመለክታል፤ ስለ ሌላው ሰው መብት ወይም ጥቅም መሟገት ማለት ነው።፡በሮሜ 8:34 ላይ ያለው ሰዋሰዋዊ ቅርጽ (Present Active Indicative) የሚያሳየው ተግባሩ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ነው። ይህም ክርስቶስ በአብ ፊት ስለ እኛ ያለው መገኘት ራሱ ዘላለማዊ ማረጋገጫ መሆኑን ያሳያል። ጳውሎስ በሮሜ 8 ላይ "ከእንግዲህ ኩነኔ የለባቸውም" ከሚለው ሐሳብ ጋር የተያያዘ ነው። አራት መከራከሪያዎችን ያቀርባል፡ ክርስቶስ ሞቷል፣ ተነስቷል፣ በአብ ቀኝ ተቀምጧል፣ ደግሞም ይማልዳል።

አማላጅነቱ የሚከናወነው "በእግዚአብሔር ቀኝ" ሆኖ ነው። ይህም ልመናው እንደ ተገዢ ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን መሆኑን ያሳያል። የብሉይ ኪዳን ካህናት ደጋግመው መሥዋዕት በማቅረብ ይማልዳሉ። ክርስቶስ ግን በአንድ ጊዜ በፈጸመው መሥዋዕትነት (Hebrews 7:25) ውጤቱን ሁልጊዜ ሕያው አድርጎ ያሳያል። የበተክርስቲያን አበው የነበረ ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ (St. Cyril of Alexandria): የክርስቶስ አማላጅነት "የዕርቀ ሰላሙን ውጤት ማጽናት" እንደሆነ ይገልጻል። እርሱ የሰውነታችንን በኩራት ይዞ በአብ ፊት በመታየቱ (High Priestly Presence) እኛ በአብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረን ያደርጋል። እርሱ ሰው በመሆኑና መከራ በመቀበሉ ምክንያት፣ እኛን ለማዳን ያለው "ሕጋዊ መብት" እንደ አማላጅነት ይቆጠራል ይላል ።

## ዕብ 7÷25

Ὅθεν καὶ σῴζειν εἰς τὸ παντελὲς δύναται ζῶν προσερχομένους δι' αὐτοῦ τῷ θεῷ, πάντοτε εἰς τὸ ἐντυγχάνειν ὑπὲρ αὐτῶν.

"wherefore he is able also to save them to the utter-most that come unto God by him, seeing he ever liveth to make intercession for them" KJV

"ስለ እነርሱ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል" በ1962 በታተመ መ.ቅ

"ስለዚህ እነርሱን ለማማለድ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ስለሚኖር በእርሱ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሁሉ በፍጹም ሊያድናቸው ይችላል" እ.መ.ት በ1997 በታተመ

ወደ አውዱ መመርመር ስንዘልቅ ዕብ 7:1-10 ስለ ሊቀካህኑ መልከ ጼዴቅ ማንነት ዕብ 7:11-28 ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ምሳሌ እንደሆነ ክፍሉ ይናገራል ::የብሉይ ኪዳን ካህናት በመካከላቸው ቀጣይነት አልነበራቸውም ፣ኢየሱስ ግን ሊቀክህነቱ ዘላለማዊ ስለሆነ ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል፡፡ከአውዱ እንደምንረዳ ከሆነ ምልጃው ዘላለማዊ እንደሆነ ነው፥ ምክንያቱም ሊቀክህነቱ ዘላለማዊ ስለሆነ፣ሊቀክህነቱ ካለ ምልጃም ደግሞ አለ፡፡ስለዚህ በእግዚአብሔር በማመን በኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኛነት በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን በአማላጅነት ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡ሊያማልድ የሚለው የግሪክ ቃል <u>ኢንቱግካነይን</u> የሚል ሲሆን ፣በማለዳ ገስገሶ ፈርደኛውን ነጻ ከማውጣት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ሊያማልድ ብሎ ሊያድናቸው ይችላል ይላል ፣ከላይ እንዳየነው በመካከለኛነት በምልጃ አልያም በሚያማልደው በኩል ነው የሚያድነን፡፡በሚያማልደው ያድነናል ስንል እንደ ፈሰሰው ደም በአብ ፊት በመታየቱ ነው፤ ኢየሱስ በውክልና ስለእኛ በአብ ፊት ይታይልናል፡፡

> "ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰሩት የእውነተኛይቱ ምሳሌ፣ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባም ፣ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለእኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ" ዕብ 9:24

በመሠረቱ እኛ ማመን የሚገባን ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ቀኝ ሆኖ ቁጭ ብሎ፣ብድግ እያለ ሳይሆን የሚያማልደው አንደ ያፈሰሰው ደም በአብ ፊት ከአቤል ደም ይልቅ ምህረት ለእኛ እንዲደረግ አብዝቶ ስለ ምጮኸ እንደ አማላጅ ሆኖ ይታያል :: ስለዚህ ከአማላጅ ተግባራት ውስጥ በአምላክ-ሰው ግብር አሁን እየፈጸማቸው ያሉት የክርስቶስ ሥራዎች :-ኃጢአትን ይቅር ማለት፣በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል ግንኙነትን ማስፈጠር ነው :: እግዚአብሔር አብ እኛን የሚያየን በቀጥታ ሳይሆን መካከለኛ በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል ነው፡፡በአሁን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ በአብ ፊት እየታየ(እየማለደ) ይገኛል፤እርሱ የሚማልደው ብቻ ሳይሆን ጠባቂያችን ጭምር ነው፡፡ ኃጢአታችን የሚሰረይልን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡1ዮሐ 2:12 እዚህጋ ምናልባት ጥያቄ ሊነሳ ይችላል ኢየሱስ ክርስቶስ የማዳኑን ሥራውን በመስቀል ላይ ሆኖ ስለ ጨረሰ "ተፈጸመ " ብሎ የለም ? ታዲያ የመዳን ሥራ ከተፈጸመ

በኋላ ምልጃ አለ ? ተብሎ ጥያቄ ቢነሳ ኢየሱስ ተፈጸመ ያለው በምድር ላይ የፈጸመው የማዳን ሥራ እንጂ ከትንሳኤ በኋላ ስላለ አገልግሎት አይደለም ።
ተፈጸመ ያለው ለሰው ልጅ ኃጢአት በመስቀል ላይ መሞቱን ፣መከራ መቀበሉና የመዋጀቱን ሥራ ተልዕኮ የመጣውን መፈጸሙን እንጂ የምልጃ ሥራ ወይም መካከለኛነቱን ማቆሙን አይደለም፡፡አንድ ጊዜ በገዛ ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቷል ፡፡ዕብ 10:25-26
"ክርስቶስ ግን ለሁልጊዜ የሚሆነውን አንዱን መስዋዕት ካቀረበ በኋላ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል" ዕብ 10:12 በሰማይ ሆኖ ስለእኛ ይማልዳል ሲባል በመስቀል ላይ የፈጸመውን ይደግማል ማለት ሳይሆን በመጋረጃው ማለትም በሥጋው በኩል የገዛ ደሙን ይዞ በመግባቱ ያ ደም እንደ አማላጅነት በአሃዱ-ሥሉስ አምላክ ዘንድ ይታያል ደግሞም ይጮኸል ማለት ነው ። የአቤል ደም ወንድሙን እየከሰሰ ከምድር ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል ፣ፍረድልኝ እያለ፤ የኢየሱስ ደም ግን በቀራንዮ የፈሰሰ ከቅድስተ ቅዱሳን ከአቤል ደም ይልቅ ማርልኝ እያለ አብዝቶ ይጮኻል ። ዕብ 12:24 የኢየሱስ ደም ከየትኛውም ሌላ ደም ይልቅ ዋጋው እጅግ ውድ ነው፡፡ምክንያቱም እንደ በጎች፣ኮርማዎች ደም ኃጢአትን የሚሸፍን ሳይሆን የሚያጥብ ነው፡፡በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ዓይነት ደሞች አሉ ለምሳሌ የአቤል ደም ማቴ 23:35፣የቅዱሳንና የነቢያት ደም ራዕይ 16:6፣የዘካርያስ ደም ማቴ 23:35፣የጻድቃን ደም ኤር 4:13 የበሬ፣ የኮርማዎች ፣የፍየልና የጥጃ ደም (ዕብ 10:4) እነኝህ ሁሉ ኃጢአትን ማጠብ ዕዳን መክፈል አይችሉም ከኢየሱስ ደም በቀር የእኛን ኃጢአት ሊያጥብ የሚችል ነገር የለም ።ምናልባት የአቤል ደም እንደፈረደለት በመጠኑ ቢሆንም የመጮኸ አቅም ሊኖረው ይችላል፤እንዲሁም የነቢያትና ጻድቃን ደም፡እነዚህ ሁሉ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ስታዩ በአዳም ኃጢአት የተበከሉ(corrupted) ናቸው፡፡የሰማዕታት ሆነ የቅዱሳን ደም በእግዚአብሔር ፊት የተበከለ ስለሆነ ማንንም ማዳን ሆነ አማላጅ ሊሆኑ አይችሉም፤ለራሳቸው አማላጅና አዳኝ ያስፈልጋቸዋል ።የቅዱሳን ደም ሆነ የሰማዕታት ደም ማንንም ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ አልቻለም ፣ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር ማስቀረብ የቻለ የኢየሱስ ደም ብቻ ነው፡፡

"በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ ለኪዳኑም
ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር እንደ ነበራችሁ አስታውሱ፡፡ አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አሁን በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል፡፡' ኤፌ 2:12-13 የኢየሱስ ደም በእግዚአብሔር ፊት ውድና እጅግ የከበረ ነው፤ ከእግዚአብሔር አብ ጋር የታረቅነው በደሙ አማካኝነት ነው፡፡ 1ጴጥ 1:18 - 19 ዕብ 9:22 17:11-14 ኢየሱስ አሁን እያከናወነ ባለው ምልጃ ደግሞ ከደረስንበት ጽድቅ እንዳንወድቅ ወደ ቀድሞአችን ኃጢአት ባርነት እንዳንመለስ እርሱን ወደ ፍጹም ሙላት ደርሰን የተዘጋጀልንን የዘላለም ርስት እንድንወርስ ዕለት ዕለት ያግዘናል፡፡ ምልጃው ዘላለማዊ ስለሆነ እኛም የሚያስጨንቀን ነገር ሁሉ ወደ እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንድናቀርብ መጽሐፍ ቅዱስ ያዘናል፡፡ ከሁለት ሺህ አመት በፊት ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቃየ፣ የተገረፈ፣ የተተፋበት፣የተሰቀለ ያ መከራ፣ ዕመሙ ስቃዩ እንደ አማላጅነት

በአብ ፊት ይታያል፡፡ስለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ቋንቋ ኢየሱስ ተማላጅ (የሚማለድ) ሳይሆን አማላጅ (የሚማልድ) የሚለው፡፡

## አምላክነቱና አማላጅነቱ

ብዙዎች ኢየሱስ አምላክ ስለሆነ በፍጹም አማላጅ አይደለም ስሉ ይደመጣሉ፡፡ አየሱስ አምላክ ነው ማለታቸው ትክክል ሆኖ ሳለ አማላጅ አይደለም ማለት.ግን ስህተት ነው፡፡ እነርሱም እግዚአብሔርን ያከበሩ መስሎአቸው ኢየሱስ አይማልድም ይላሉ፡፡በሌሎች ኃይማኖቶች ያሉ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነ፤በልተዋል ፤ጠጥተዋል ፤ደክሞአል ፤ ተሰቅሎአል፤ሞተአል ተነሥቶአል ስንላቸው አምላክ ከሆነ እንደት ይራባል ? እንዴት ይጠማዋል ? እንዴት ይደክማል ? እንዴት ይሰቀላል ? እንዴትስ ይሞታል ? በማለት በራሳቸው ጥበብና መሥመርት መቀበል ያዳግታቸዋል ፡፡ ይህንንም የሚሉት አምላክ እንዴት እንድህ ያደርጋል ? በፍጹም ለአምላክ የሚገባ ገጸባሕርይ አይደለም ብለውት ስለሚያምኑት ነው፤አምላክን እንዴ ማዋረድ ስለምቆጥሩትም ጭምር ነው፡፡ ነገር ግን ያልገባቸው ነገር ኢየሱስ ክርስቶስ የተራበ የተጠማ የሞተና የተንከራተተ በመለኮት ባሕርይ ይህ ስለነበረበት ሳይሆን የሰው ልጅ ካለበት ፍዳ ለማውጣትና ለባርነት የተሸጡትን ለመዋጀት መለኮት ከትስጉት(ሥጋ) ጋር ስለተዋህደ ነው፡፡በዘመናችም አንዳንድ ቤተ-እምነቶች ኢየሱስ ክርስትስን ያከበሩ መስሎአቸው ሥጋ በመዋሐዱና ሰው በመሆኑ ምክንያት የተሰየመባቸውን ስያሜዎች እያጠፉ ይገኛሉ፤ኢየሱስ አማላጅ ነው ሲባል እንደመናፍቅነት ይቆጥራሉ ፡፡አክሎም ኢየሱስ የማለደው በሥጋ ወራት ነው እንጂ ካረገ በኃላ አይደለም ይላሉ፡፡እነረሱ  እንድ ይበሉ እንጂ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት ብቻ የማለደ ሳይሆን አሁንም በአብ ቀኝ ሆኖ ይማልድልናል፤ለምን ቢባል በምድር ላይ ስኖር ብቻ ሳይሆነ ሰው የነበረ ፤ካረገ በኃላም ፍጹም ሰው ነው፡፡ ኢየሱስ ካረገ በኃላ ሰው እንደ ነበረ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻሐፈው መልዕክት ላይ የገልጻል፡፡

"አንድ እግዚአብሔር አለና ፤ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ ፤እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" 1ጢሞ 2፡5

እርሱ ፍጹም ሰው ብቻ ሳይሆን ፍጹም አምላክም ጭምር ነው፡፡እርሱም አምላክ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፡፡ኢየሱስ ከአብ ጋር የነበረ የዘላለም አምላክ ነው፡፡ዮሐ 1፡1-2፤ፊል 2፡6፤ራእይ 1፡1፤ሮሜ 9፡5፤1ዮሐ 5፡20፤ ሚክ 5፡2

- ሁሉን ቻይ( ከሃለ ኵሉ) ነው ፊል 2፡9-10
- በሁሉም ቦታ አለ(ከሳቴ ኵሉ) 2ቆሮ 2፡14፤ሮሜ 11፡36

- ፈጣር (ገባሬ ኵሉ) ነው ዮሐ 1፡3፤ሮሜ 11፡36፤ዕብ 1፡10-12
- ዘላለማዊ የሆነ (እምቅድመ ዓለም) ኢሳ 9፡6፤ሚክ 5፡2
- በሁሉም ላይ ሥልጣን ያለው (ዘሥሉጥ ላዕለ ከዱ)

ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ሁሉ ፍጹም ሰው መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ከተባለ ከአብ ያንሳል ብለን ማሰብ የለብንም፤ምክንያቱም ከሥራ ክፍፍል የተነሳ ማነስ(functional subordination)ና ከማንነት የተነሳ ማነስ (ontological subordination) ስለምለያይ ነው፡፡እርሱ በሥራ ክፍፍል በገዛ ፍቃዱ አነሰ እንጂ በማንነቱ አላነሰም ከአብ ጋር አንድ ነው እንጂ ፡፡ዮሐ 10፡30፤ፊል 2፡6-8
በእኛና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ ሆኖ የቆመ አምላክ ብቻ በመሆኑ ሳይሆን አምላከ-ሰው(God-Man) በመሆኑ ነው፡፡መካከለኛና አማለጅ በመሆኑ አምላክነቱን አይቀንስም ደግሞም አያስቀርምም ፡፡ስለዚህ እኛ በምስጋናና በልመና ሆነን በምልጃ ወደ እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስንቀርብ ጸሎታችን ተሰሚነት እንዲኖረው በአባቱ ፊት ስለ እኛ ብቁ ሆኖ የሚታይ አማላጅ ነውና፡፡ኢየሱስ አማላጃችን ብቻ ሳይሆን የነፍሳችንም መልሕቅ ነው፡፡መልሕቅ ከብረት የተሠራ የመርከብ ማቆምያ ሲሆን ሀይለኛ አውሎንፋስ ስሜጣ መርከቡ እንዳይሰበር ያደርጋል ዕብ 6፡19-20 ፡፡ማሕበሉ ነፋሱ እንዳይጥላቸው መልሕቃቸውን ወደ ጥልቁ ባሕር ይጣላሉ፤ ለእኛም የሕይወታችን ሊቀካህንና መልሕቃችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡በመስቀሉ ካስታረቀን በኃላ በዚህ ዓለም ማዕበል እንዳንወሰድ አጽንቶ የያዘን ሊቀካህናችን እርሱ ነው፡፡ዕብ 7፡20-28፤ ዘካ 6፡12-13፤ኢሳ 11፡10-11 ስለዚህ ስለ እኛ ሊያማልድ በሕይወት ይኖራል ሲል በድካማችን ልያግዘን ጸጋውን ሊሰጠን እንደሆነ አስቀድሞ እንድህ በማለት ተናግሯል ፡- "እንግዲህ ወደ ሰማያት ያረገ ታላቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ፣እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ፡፡በድካማችን የማይራራልን ሊቀ ካህናት የለንምና ነገር ግን እንደ እኛ በማንኛውም ነገር የተፈተነ ሊቀ ካህናት አለን፤ ይሁን እንጂ ምንም ኃጢአት አልሰራም " ዕብ 4፡14-16

## ኢየሱስ በትስብዕነቱ ብቻ ሳይሆን በአምላክ-ሰውነቱ ነው ምልጃው

በመጀመሪያ ኢየሱስ በትስዕግቱ(በፍጹም ሰውነቱ) ብቻ ሳይሆን በአምላክ-ሰው ማንነቱ ነው ምልጃው የሚለው ግልጽ እንዲሆንላችሁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በጥቂቱ ላውጋችሁ፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም (ምሉዕ) ሰው ፍጹም አምላክ ነው፡፡በመጀመሪያ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት አብረን እንቃኝ

"በመጀመሪያ ቃል ነበር ፤ቃልም ከእግዚአብሄር ጋር ነበር፤ቃልም እግዚአብሔር ነበር፤እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር.......ቃልም ሥጋ ሆነ ፡፡"ዮሐ 1፡1-2፡14

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ምርት በእጁ ብዕርን ይዞ ከብራናው ጋር ስያላትም ስለ ኢየሱስ ከድኅርት ሕይወቱ ሳይሆን ከቅድመ ሕይወቱ ይጀምራል ፡፡በመጀመሪያ ቃል ነበር የሚለው እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለም ከመፍጠሩ በፊት ቃል(ሎጎስ) እንደነበረ ነው፤ይህም በጊዜ ሳይወሰን ለዘላለም ይኖር ነበር፡፡ቃልም እግዚአብሔር ነበር ....ቃልም ሥጋ ሆነ፡፡ከክፍሉ እንደምንረዳው ከሆነ ቃል ወይም በግርኩ ሎጎስ የሚለው የሰው ንግርት ቃል ሳይሆን አካላዊ ቃል እኔነት ያለው ነው፡፡በመጀመሪያ የነበረ ቃል እግዚአብሔር እንደነበረ ፤እግዚአብሔር የነበረ ቃል ቍጥር 14 ላይ ሥጋ (ሰው) እንደሆነ ያመለክታል ፡፡ቃል ሥጋ የሆነ እንደሚታወቀው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ስለዚህ በግልጽ ክፍሉ የኢየሱስ አምላክነት ይመሰክራል፡፡

« እኔ እና አብ አንድ ነን »ዮሐ 10፡30

ይህም በባሕርይ አንድ እንደሆኑ ይገልጻል ፤አብ በባሕርዩ አምላክ ከሆነ ፣ወልድም ከአብ ጋር በባሕርይ አንድ ከሆነ ፣ ወልድ እራሱ አምላክ ነው ማለት ነው፡፡

" አባቶች ከእነርሱ ናቸውና ፤ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ እርሱም ከሁሉምበላይ ሆኖ ለዘላለም የተባረከ አምላክ ነው፡፡" ሮሜ 9፡5

"እርሱ በባሕርዩ አምላክ ሆኖ ሳለ ፤ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን ሊለቀውእንደማይገባ አድርጎ አልቆጠረውም ÷ነገር ግን የባርያ መልክ ይዞ ፤በሰውአምሳል ተገኝቶ ራሱን ባዶ አደረገ ፤ሰው ሆኖ ተገልጦም ራሱን ዝቅ አደረገ፤እስከ ሞት ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ታዛዥ ሆነ ፡፡'ፊል 2፡6-8

ክፍሉም አሁንም የሚያሳየው እርሱ በባሕርይ አምላክ ወይም በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ የሚለው በባሕርይ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ፤እንዲሁም የባርያ መልክ ይዞ በሰው አምሳል ተገኝቶ የሚለውም ፍጹም ሰው መሆኑን

ያመለክታል ፡፡ማቴ 1፡23፤ዮሐ 10፡26-30፤14፡7-9፤ዕብ 1፡7-8፤ዮሐ 1፡23፤ራእይ 20፡28፤21፡5-7ስለ አምላክነቱ በአጭሩ ማየት ከቻልን ስለ ፍጹም ሰውነቱ አብረን እንቃኝ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ሁሉ ፍጹም ሰው ነው፤ይህም « ቃል ሥጋ ሆነ » የሚለው የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑን ስያመለክት ምስጢረ ሥጋዌ ብለን እንጠራለን ፡፡ይህ ምስጢር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ በመወለዱ አምላክነቱን ሳይለቅ አምላክ ሰው የሆነበት ልዩ ምስጢር ነው፡፡መንፈስ ቅዱስ በድንግል ማርያም በጸለለ(በከበበ) ጊዜ መለኮት ከሥጋ ጋር ተዋሐደ፡፡አካላዊ ቃል አምላክነቱን ሳይለቅ ከአንድ አካልነት ወደ ሁለት አካልነት ሳይመጣ ፍጹም ሰወ ሆነ፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጹም አምላክነቱ የጊዜ ቀመር ሳይኖር ከአብ ከዘላለም ተወለደ ፤ይህም ከብርሃን የተወለደ ብርሃን፣ከመለኮት የተወለደ መለኮት፣ከአምላክ የተወለደ አምላክ ያልተፈጠረ የተወለደ ፣ያልሰረጼ(Processed) ግን የተወለደ፣ያልተቀደመ ያልቀደመ አምላክ ነው ፡፡መዝ 2፡7፤109፡3 ኢየሱስ ክርስቶስ የጊዜ ቀመር እያለ (ድኅራዊ) ከድንግል ማርያም ተወለደ ፡፡ኢሳ 7፡14፤9፡6፤መዝ 106፡20፤ገላ 4፡4 ከቅድመ ዓለም ግን ያለእናት ከአብ ተወለደ፡፡

የመለኮት ባሕርይ የሰው ባሕርይ በአንድ አካል ሲኖሩ ባሕርያቸውን አልለወጡም ፣አንደኛው ባሕርይ ወደ ሌላኛው አልተለወጠም ፣አንደኛው ሌላኛውን አልተጫነም ፣ እርስ በርሱም አልተቀላቀሉም ወይም ወደ ሌላ ሦስተኛ ባሕርይ አልተለወጡም፡፡ፍጹም ሰውነቱ ወደ ፍጹም አምላክነቱ አልተቀየረም ፥ፍጹም አምላክነቱ ወደ ፍጹም ሰውነቱ አልዞረም፡፡ረቂቅ መለኮት ርቀቱን ሳይለቅ ፥ ግዙፍ ሥጋ ግዙፍነቱን ሳይለቅ ማለትም ግዙፍ ሥጋ ረቂቅ መለኮትን ግዙፍ ሳያደርግ ፥ ረቂቅ መለኮት ግዙፉን ሥጋ ሳያረቀው ተዋሐዱ ማለት ነው፡፡እያንዳንዱ ባሕርይ የራሱን ምንነት እንደያዘ ያለመጨመር ፥ያለመቀነስ ፥ያለመቀዋወም በአንድ ማንነት(አካል) ውስጥ ይኖራሉ፡፡ሁለቱም ባሕርያት ለዘላለም በአንድ ሕላዌ ይኖራሉ፡፡አምላክ-ሰው የመሆኑ ምስጢር ሥጋና ነፍስ ተዋሕደው ኖሮው በሞት ሰዓት እንደሚለያዩትም ሳይሆን ያለመለያየት ነው ፡፡ሥጋ በሠራ ሥራ መለኮት ለአንድት ማይክሮሰከንድ አልተለየም፥መለኮት በሠራ ሥራ ሥጋ ለአንዲት ማይክሮሰከንድ ፈጽሞ አልተለየም ፡፡መለኮትም ከተሰብእት ጋር ከተዋሐደ በኃላ ከሥራ በማንኛውም ሥራ አንድነታቸው ፈጽሞ አልተለያየም ፥መለያየት የለባቸውምና ፡፡ለመለኮት ጥንት እንደሌለው፥ከትንሣኤ በኃላ ለትሰብእትም እንዲሁም ፍጻሜ የለውም፡፡የመለኮት የትስብዕት ተዋሕዶ ያለመደራረብ ነው ይህም ልብስ በልብስ ላይ እንደሚደራረበው ሳይሆን ያለመደራረብ ነው፡፡

ዮሐ 1፥1-18፤3፥18፤1ቆሮ 8፥6 ከእነዚህ ክፍሎች እንደምንረዳው የቃል ባሕርይ የሥጋ ባሕርይ ወደ መሆን ፥ የሥጋ ባሕርይም የቃል ባሕርይ ወደ መሆን አልተለወጠም ፤ሁለቱም ባሕርያት ያለመለዋወጥ ፥ባለመቀላቀል ጸንቶ የኖራሉ፡ ፡በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ የትስብዕት ፍቃድ የመለኮት፥የመለኮት ፍቃድ የተስብዕት ነው፥ላይለያዩ ተዋሕዶአልና ፡፡

የጥንት ቤተክርስቲያን አበው የነበረ ኤጲፋንዮስ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውነት ፍጹም አምላክነቱ ያለመለዋወጥ ፥ያለመለያየት ስያስረዳ

እንዲሁም የቤተክርስቲያን አበው የነበረ አትናቴዎስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስናገረ

> "አሁንም በተዋሕዶ ሰው የሆነ አምላክ እንደሆነ ሰምተህ ዕወቅ ፥አምላክ ብቻ ከሆነማ እንደምን በታመመ ነበር ? ይህ ሥራ ( ሕማሙ፣ሞቱ ) ከእግዚአብሔር የራቀ ነውና (ዘዳ 32፥40) ፤ ሰው ብቻ ከሆነ በታመመ ፣በሞተ ጊዜ ሞትን እንደምን ድል በነሣው ነበር ? ሌሎችንም በነፍስ በሥጋ እንደምን ባዳነ ነበር ? ይህ ከሰው ኃይል በላይ ነውና፡"[9]

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፈጹም አምላክ ቢሆንም አንድ ክርስቶስ እንጂ ሁለት አይደለም፡፡በብሉይ ኪዳን ሊቀካህናት የሚሆኑት ሰው ብቻ ስሆኑ የአዲስ ኪዳን ሊቀካህን ልዩ የሚያደርገው ፍጹም ሰው ብቻ ሳይሆን ፍጹም አምላክ በመሆኑ ጭምር ነው ፡፡ፍጹም ሰው የሆነው ሊቀካህናት ስለሚያስፈልገን ስለእኛ ልክ እንደእኛ በደምና በሥጋ ተካፈለ፡፡ ዕብ 2፥14 ሰውነታችን ስለተካፈለ መከራና ስቃይ ስለሚያውቅ ሰለእኛ ይማልዳል ፡፡ይህን ያህል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በጥቅቱ ካየን አሁን ደግሞ በእርሱ የተሠራ ሥራ (subordination functions) እንደማይነጣጠል እናያለን ፡፡ኢየሱስ በዚህ ምድር እያለ ተጠማው ሲል የተጠማው በፍጹም ሰውነቱ ነው ወይም በሥጋዬ ተጠማው አላለም ፤ሲርበው በሥጋዬ ነው አላለም፥ኃጢአትህ ይቅር ተብሎልሃል ሲል ይቅር ያልኩት በአምላክነተ ነው አላለም፡፡በክርስቶስ ኢየሱስ የተሠራ ሁሉ በአንዱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተሠራ እንጂ በመነጣጠል አንድ ጊዜ በሰውነቱ አንድ ጊዜ በአምላክነቱ አልተደረገም ፡፡በባሕር ላይ እየተራመደ ወደ ደቀመዛሙርቱ ስሄድ እዚህጋ አምላክነቱን ተጠቅሞ ነው አንልም፤ይልቁንም በባሕር ላይ መራመድ የማይችል ተሰብእት በተዋሐደው በመለኮት ጠባይ በባሕር ላይ ተራመደ እንላለን ፡፡በተስብእቱ የፈጸመው ሥራ በመለኮትነቱ እንደተፈጸመ ተቆጥራል ፡፡1ቆሮ 2፡8፤ገላ 2፡20፤ሐዋ 20፡28 በመለኮት የፈጸመው ሥራ በተሰብእት እንደተፈጸመ ተቆጥራል ፡፡ማቴ 9፡6፤12፡8፤ 24፡29-31፤25፡31-34፤ዮሐ 3፤13፤6፡62፤ሐዋ 7፡57 በመለኮት መጠሪያ ሳለ በሰው ግብር፣በሰወ መጠሪያ ሳለ በመለኮት ግብር ተገልጾአል፡፡የተሠራ ሥራ በአምላከ-ሰውነቱ( unified subject) ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በትስብዕነቱ(በፍጹም ሰው) ሳይሆን በአምላክ-ሰውነቱ (በፍጹም ሰው በፍጹም አምላክ) ነው የሚማልደው ስንል ፍጹም ሰውነቱን ከፍጹም አምላክነቱ ፥ፍጹም አምላክነቱን ከፍጹም ሰውነቱ ስለማይነጣጠል ስለማይለያይና ስለማይደባለቅ ነው፡፡ይህንን በሰውነቱ ነው የሰራ ፥ያንን ደግሞ በአምላክነቱ ነው የሠራ አንልም ፡፡ የሁለቱ ባሕርያት ጥምረት በአንዱ በክርስቶስ ውስጥ ያለመነጣጠል ያለመደባልቅ ስላሉ ነው፡፡የቀድሞ አቤዎች ስለ ኢየሱስ ፍጹም ሰውነቱ ፍጹም አምላክነቱ ምሳሌ ስጠቀሙ አንድ ብረት በፍም እሳት ውስጥ ብንከት ከጋለ በኃላ

ከእሳት ውስጥ ብናወጣ እሳት ወይም ብረት አንልም ይልቁንም የጋለ ብረት እንጂ ፤ከእሳት ውስጥ ካወጣን በኃላ እሳት አልያም ብረት እንደማንልና ስሙ ተቀይሮ የጋለ ብረት እንደምንል ሁሉ ፣የጋለ ብረት ስመታ ብረት ወይም እሳት ተመታ አንልም ይልቁንም የጋለ ብረት ተመታ እንላለን ምክንያቱም ብረት በጠባዩ ተመች ሲሆን የማይመታ እሳት በብረት ጠባይ[9] በኩል ተመታ እንላለን ፡፡ኢየሱስ ሲርበው በሰውነቱ ተራብ አንልም ፥የማይርበው መለኮት በሥጋ

ጠባይ በኩል ተራብ እንላለን፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰገረፍ ስሰቃይ ለዓለም መከራ ስቀበል ስሞት በፍጹም ሰውነቱ ነው አንልም ነጣጥለን ይልቁንም መከራ ሥቃይ መገረፍ የማያውቅ መለኮት በሥጋ ጠባዩ መከራና ስቃይ ተቀበለ፥ማይገረፍ መለኮት በሥጋ ጠባዩ ተገረፈ፥የማይሞተት መለኮት በሥጋ ጠባዩ ሞተ እንላለን ምክንያቱም ሥጋ በጠባዩ ማች ስለሆነ፡፡መለኮት በባሕርይው [10]አይሞትም ፥የማይሞተው አምላክ የሞተው ከሚሞተው ከሰወ ባሕርይ ጋር ተዋሕዶ ስለ ነበረ ነው ስለዚህ አምላክ በሥጋ ጠባይ ሞተ እንጂ መለኮት በባሕርይ አልሞተም ፡፡ከግብር አኳያ ሰውነቱና መለኮትነቱን ነጣጥሎ መናገር አይቻልም ፡፡እኛ ለኢየሱስ ስንሰግድ ለአምላክነቱ እንጂ ለፍጹም ሰውነቱ አንሰግድም ብለን አንነጥልም፡፡ይልቁን የማይሰገድና ማይመለክ ሥጋ በመለኮት በኩል ተመለከ እንላለን፡፡ሰለዚህ የድነት ሆነ የአማላጅነት ሥራ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ማለትም በአምላክ-ሰውነቱ ያደረገ ሥራ እንጂ ነጣጥለን በትስብዕነቱ የተሰራ ነው አንልም ፡፡መለኮት በሥጋ ጠባዩ ማለደ፡፡ኢየሱስ የሚማልደው በአምላክ -ሰውነቱ ነው!!!

## ከትንሣኤ በፊትና ከትንሣኤ በኃላ የተደረገ ምልጃ ልዩነቱ

ክርስቶስ በምድር እያለ የማለደ ምልጃና ወደ አባቱ ካረገ በኃላ እየማለደ ያለ ምልጃ ይለያያል ፡፡ከትንሣኤ በፊት የማለደ ምልጃ በግሪኩ "aphie'mai/ፊሄማይ" የሚል ሲሆን ትርጉሙም ይቅር በል ፣ምህረት አድርግ ፣ቻል አድርግ ማለት ነው፡፡ለምሳሌ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በግርክ aphe's በላቸው፡፡ "ሉቃ 23፡34

እንዲሁ ሉቃ 22፡32 «...እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ...»

‹‹…But I have prayed for thee…››KJV bible

‹‹..de'ego' de'mai peri soo…››Greek bible translation

ከትንሣኤ በፊት አማለደ የተባለ ለመኔ ወይም ጸለዪ የሚል ትርጉም ስኖረው ከትንሣኤ በኃላ ግን entyncha'no'/ኢንቲካሀኖ የሚል ስሆን ትርጉሙም አበቱታ ማቅረብ በፍርድ ቤት ዳኛ ፊት ይግባኝ ማለትን ያመለከታል ፤ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ እያለ የማለደ ምልጃና ካረገ በኃላ እየማለደ ያለ ምልጃ ይለያያሉ፡ ፡ስናጠቃልሎ ከትንሣኤ በፊት የማለደ ምልጃ መለመን ወይም መጸለይ የሚል ትርጉም ስኖረው ከትንሣኤ በኃላ የማለደ ምልጃ ግን አበቱታ ማቅረብ ይግባኙን መጠየቅ ነው፡፡

---

9 ጠባይ ማለት የባሕርይ ግብር ስሆን ባሕርይ ማለት ግን ጠባይ ማለት አይደለም፣ጠባይ መቀየር ብችልም ባሕርይ ግን አይቀየርም ፡፡ የወድና የሴት ማንነት ወይም ባሕርያቸው ሰው ናቸው ፤ሰው መሆናቸውን መቀየር አይችሉም ፣የመናደድ ጠባይ መቀየር ብችሉም ፡፡

10 ባሕርይ የማንኛውም አካል መሠረት ነው ፥ ባሕርይ የሚለው ሥረው ቃሉ ባሕር ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ባሕር በውሃ ውስጥ ለሚኖሩ ሕይወት ላላቸው ፍጥረታት መሠረት እንደመሆኑ እንዲሁም የአካል መሠረት ነው፡፡

## ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ከሆነ እንደት ፈራጅ ሆነ ?

ይህ ጥያቄ የሚነሣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት ያልተገነዘበ ጎልና የተነሳ ይመስላል፡፡በመጀመርያ መገንዘብ ያለብን ነገር ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ (አምላከ-ሰው) መሆኑን መረዳት ይጠበቅብናል፡፡ ኢየሱስ የሰው ልጅ በመሆኑ እግዚአብሔር በሰዎች ላይ እንድፈርድ ሥልጣንን ሰጥቷል፡፡

« ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድም ሰው ስንኳ አይፈርድም፡፡»ዮሐ 5፡22-23 እንድፈርድ ሥልጣንን እግዚአብሔር አብ ለእግዚአብሔር ወልድ የሰጠበት ምክንያት የሰው ልጅ በመሆኑ የሰውን ልብ ያውቃል ፤እርሱም ምሉዕ ሰው ስለሆነ የሰዎችን ድካም ሆነ ስሜታቸውን ስለምረዳ ነው፡፡ስለ ፍርድ ስናነሳ ፍርድ ወይም መፍረድ የሚለውን የቃሉ ትርጉምና ስለ ፍርድ ዓይነቶች ማወቅ ይጠበቅብናል ፡፡እስከ ወደ ቃሉ ትርጉም እንሂድ፡-መፍረድ/ condemnára የሚል ቃል ከላትን com/ኮምና damnár/ዳምናር ከሚለው ሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን በግሪክ katakrino/ካቲአክርኖ የሚል ደግሞ ካታ(kata)[11]ና ክርኖ(kpivw) ከሚል ሁለት ቃላት የተገኘ ነው ትርጉሙ ፈረደ፡የሚፈርድና ፈራጅ የሚል ነው፡፡በዕብራይስጥ ሻውፋት[12] ወይም ምሽፓውት የሚለው ከግሪኩ ጋር ተመሳሳ ትርጉም አለው፡፡የቃሉን ትርጉም በዚህ መልኩ ካየን የፍርድ ዋና ሀሳብ እውነትን ከእውሸት ለመለየት ነው፡፡በእኔ አመለካከት ፍርድ ከዓይነቱ አንጻር በዋናነት በሦስት ይከፈላል፡፡

1.የፍትህ ፍርድ 2.የተግሣጽ ፍርድ 3.የሕይወት ትንሣኤና የሞት ትንሣኤ ፍርድ

የመጀመርያ የፍትህ ፍርድ የምንለው በበዳዩና በተበዳዩ መካከል እግዚአብሔር በመዳኘት በዳዩን በቅጣት ተበዳዩን በማጽናናትና በመካስ የሚፈርድ ሲሆን ይህም የፍትህ ፍርድ ይባላል፡፡ዮሐ 8፡1-11፤አሞጽ 6፡12-14፤ኤርም 25፡29፤ 1ቆሮ 5፡4-5 የተግሣጽ ደግሞ ከአለም ጋር እንዳይፈረድብን እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚገስጸን ነው፡፡1ጴጥ 4፡14፤ ዕብ 12፡5፤2ቆሮ 7፡9

ሦስተኛው የዘላለም ሕይወትና የዘላለም ሞት ፍርድ የምንለው የመጨረሻ ፍርድ በመባል ይታወቃል፡፡ ከፍትህና ከተግሣጽ ፍርድ የሚለየው ሁለቱ ከትንሣኤ በፊት የሚፈጸሙ ሲሆኑ ይህ የመጨረሻ ፍርድ ግን አንዳንዶች ለዘላለም ሕይወት ሌሎቹ ደግሞ ለዘላለም ሞት ከትንሣኤ በኃላ የሚፈጸም ነው፡፡ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እየፈረደ ያለው የመጨረሻ ፍርድ ሳይሆን የፍትህና የተግሣጽ ፍርድ ነው፡፡ማወቅ የሚገባን ነገር ኢየሱስ የሚማልደው ለፍትህ ወይም ለተግሣጽ ፍርድ ሳይሆን ከደረስንበት ጽድቅ እንዳንወድቅ የመጨረሻ ሞት ፍርድ እንዳይፈረድብን እስከ መጨረሻ መጽናት እንድንችል ነው፡፡

---

[11]kata against or down.[12]Shaw'fat mean Judgement, damnation, condemnation, right, lawful, and custom.

ምልጃው ከኃጢአት አንጻር ነው እንጂ ከፍትህ ወይም ከተግሣጽ አንጻር አይደለም፡፡በአሁን ጊዜ በማንም ላይ የመጨረሻ ፍርድ አልተሰጠም፤ይልቁንም አሁን ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የዘላለም ሕይወት እንድያገኙና ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንድቀላቀሉ የምስራቹ እየተሰበከ ያለ ወቅት ነው፡፡

> ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም ፥ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል፡፡1ጴጥ 3፥9
>
> እንዲሁም
>
> እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ
> ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ቀን ቀጥሮአልን ፥በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው
> እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ስለዚህም እርሱን ከሙታን
> በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል፡፡ ሐዋ 17፥30-31

የመጨረሻ ፍርድ የሚከናወነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስመጣ ነው፡፡ዮሐ 5፡28-29 ፤ማቴ 12፡36-37፤1ጴጥ 1፡7፤ሮሜ 2፡16፤ኢሳ 2፡12፤አሞጽ 5፡18-20፤ሚል 4፡1-5

ስናጠቃልል ኢየሱስ አሁን ደሙን ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ስለገባ በአብ ፊት እየታየና እየማለደ ይገኛል እንጂ የመጨረሻ ፍርድ እየፈረደ አይደለም፡፡

ኢየሱስ አሁን እየፈረደ ሳይሆን እየማለደ ይገኛል ፥ምልጃው እስከ ፍርድ ቀን ብቻ ነው፡፡በፍርድ ቀን ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም ፥አሁን ግን አማላጅ ነው፡፡

<u>የኢየሱስ አማላጅነቱ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ፤ፈራጅነቱ  ደግሞ በፍርድ ቀን ነው፡፡</u>

## መካከለኛ

መካከለኛ የሚለው ቃል ሜስቴስ/ μεσίτης ከሚለው ግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙ ሁለት ወገኖችን ለማስታረቅ ወይም ለማገናኘት በሁለት ወገኖች መካከል የሚቆም ማለት ነው፡፡በመጽሐፍ ቅዱስ የአድስ ኪዳን መካከለኛ የሚለው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን መካከለኛ ነው ፡፡በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከሕዝቡ መካከል የሚያስነሳቸው ካህናት፥ነገስታትና ነቢያት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የማገናኛ መስመር ሆኖ አገልግሏል፡፡ ለምሳሌ ከነብያት ሙሴ ዘዳ 18፡18-22፤ዘጸ 19፥3-8፤ከካህናት አሮን ዘሌ 9፥7፤ከነገሥታት ዳዊት ሰሎሞን 1ነገ 8፥14-54 በመካከለኝነት አገልግሏል፡፡ነገር ግን በብሉይ ኪዳን መካከለኛ ሆኖ እያገለገሉ የነበሩ ሚች ስለሆኑ አገልግሎታቸው ዘላቂነት አልነበረውም፡፡የዕብራውያን ጸሐፍ ስናገር በዕብ 10፡1 « ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና ፥ሰለዚህ በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያመሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይቻልም ፡፡ »አሁን ደግሞ 1ጢሞ 2፥5 ወደ ክፍሉ አውዳዊ ትንተና እንድ፡-

### 1ጢሞ 2፥5

εἷς γὰρ Θεός, εἷς καὶ μεσίτης Θεοῦ καὶ ἀνθρώπων, ἄνθρωπος Χριστὸς Ἰησοῦς,[13]

" for there is one God, and one mediator between God and man, the man Christ Jesus "[14]

"አንድ እግዚአብሔር አለና፥በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው "[16]

"አንድ እግዚአብሔር አለና፤ደግሞ በእግዚአብሔር በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው "[17]

"እግዚአብሔር አንድ ነው ፤በመካከል ሆኖ እግዚአብሔርና ሰውን የሚያስታርቀውም አንድ ነው፤እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው "[18]

"አሐዱ እግዚአብሔር ወአሐዱ ኅሩይ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኮነ ሰብአ "[19]

አሁን ደግሞ ክፍሉን ወደ መመርመር እንዝለቅ

- አንድ እግዚአብሔር አለና( εἷς γὰρ Θεός )፡-

" እስራኤል ሆይ ስማ ጌታ አምላካችሁ አንድ አምላክ ነውና"" ዘዳ 6፡4

"የመጀመሪያውና የመጨረሻውም እኔ ነኝ፤ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም ፡፡" ኢሳ 44፡6

« ምንም እንኳን አምላክ ሳይሆኑ አማልክት ተብለው የሚጠሩ ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች በሰማይም ሆነ በምድር አሉ ቢባል የእኛ አምላክ ግን የሁሉ ነገር ፈጣርና እኛም የእርሱ የሆንን አንዱ እግዚአብሔር አብ ብቻ አለን፡፡»1ቆሮ 8፡6

- ➢ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ÷እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው( εἷς καὶ μεσίτης Θεοῦ καὶ ἀνθρώπων, ἄνθρωπος Χριστὸς Ἰησοῦς) እርሱ አምላክ ብቻ ሳይሆን ሰውም (ἀνθρώπων) ጭምር ነው

በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ይህ ክፍል በግልጽ አንድ (አሐዱ) መካከለኛ እንዳለ በግልጽ ያሰፍራል፡፡ ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ብቸኛው መካከለኛ አየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ብዙ ሊቀካህናት ተነስተው ነበር እንዳይቀጥሉ ማች ስለሆኑ አልሆነላቸውም ከአሮን ጀምሮ አንዱ አንዱን እየተካ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ደረሰ፡፡ከአሮን እስከ እየሱስ ክርስቶስ ሰማንያ ሶስት ሊቀካህናት የተሾሙት ስሆን ጌታችን ሞትን አሸንፎ የማይሞት ስለሆን ሊቀክህነቱ ዘላለማዊና ተተኪ የለለው ነው ምክንያቱም ማች ስላልሆነ፡፡ አንዳንድ ቤተእምነት ለምን ብዙ መካከለኞችን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያደርጋሉ፡፡ በእውነት መጽሐፍ ቅዱስ ላይ መጨመር አይሆንብንም? በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ ብለው ሰለእራሳቸው በመካከልኙነት የሰየማቸው ቅዱሳን ሆነ መላእክት ራሳቸውን «እኛ መካከለኞች ነን» አላሉም፡፡መካከለኛ የሆነው አንድ(አሐዱ) ብቻ ከሆነና እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሆነ መላእክት ወይም ጻደረቃን በእግዚአብሔርና በሰው መካከል በመሆን ሊያማልዱ እንደምችሉ ማሰብ ከተጻፈ ማለፍ ነው፡፡መካከለኛው ሰው ወይም መላእክት ሳይሆኑ አምላክ-ሰው ነው፡፡ ልብ ማድረግ የሚገባን ነገር ቢኖር ክፍሉ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላል ፤እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ሁሉ መካከለኛውም አንድ ነው፣ማነው ብለን እንዳንጠይቅ ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በማለት ይመልሳል፡፡እርሱም የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፡፡ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ ÷የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንድቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፡፡ዕብ 9÷15፤ዕብ 12÷24፤ዕብ 8÷6

**መካከለኛ ለመሆን ግድ እነዚህን መስመርቶች ማማላት ይጠበቅበታል፡-**

- ✓ ከሁለቱ ወገን የሆነ ወይም የሁለቱ ወገኖች ባሕርይ ያለው፡
- ✓ ሊቀካህናት ንጉሥ ወይም ነቢይ የሆነ ምክንያቱም መካከለኛ መሆን የሚችሉ በእነዚህ አገልግሎት ውስጥ ያሉ ሰዎች ብቻ ስለሆኑ፡፡

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መካከልኙነትና አማላጅነት ግልጽ እንድሆንላችሁ አንድ ምሳሌ እንጠቀም፡-

ሰወና ሰው ቢጣላ ማን ያስታርቃል ?ብባል ሰው ወይም እግዚአብሔር ብላችሁ እንደምትመልሱ እርግጠኛ ነኝ ፡፡ እንበልና ሦስት አምላክ አሉ እንበል (ለምሳሌነት እንጂ ሦስት አምላክ የለም አንድ እንጂ) ሁለቱ ቢጣሉ ማን ያስታርቃል ?ሰው አልያም ሦስተኛው አምላክ ? ሰው እንዳትሉ በአምላክ ጣልቃ ብገባ እንዳልነበረ ይሆናል ምክንያቱም ሰው ስለሆነ፡፡ስለዚህ ሰው ማስታረቅ ሆነ ማግባባት አይችልም ፥ይልቁንም ሦስተኛ አምላክ የሆነ ብቻ ነው ማስታረቅና ማግባባት የሚችለው ለምን ብባል አቻቸውና በባሕርዩ እኩል ስለሆነ፡፡ይባስ ብሎ ሰውና እግዚአብሔር ተጣሉ ማን ያስታርቃል ወይስ አማላጅ ይሆናል ?፥እዚህጋ ሰው ሆነ እግዚአብሔር አማላጅ ሆነ አስታራቂ መሆን አይችሉም ምክንያቱም የእግዚአብሔርና የሰው ባሕርይ ስለሚለያይ ስለዚህ የግድ የሁለቱም (የእግዚአብሔርና የሰው ባሕርይ) ያለው ሰው ያስፈልጋል ፡፡የሁለቱም ማለትም የአምላክ-ሰውነት ባሕርይ ያለው በሰማይ ሆነ በምድር የለም ፥ የእግዚአብሔርም የሰውም ባሕርይ ያለው አማላጅ ሆነ ማስታረቅ የሚችለው ጌታችን መድኃንታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ምክንያቱም እርሱ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ስለሆነ ሁለቱን ወገን ማግባባት ይችላል ፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳንና መካከለኛ ነው የተባለው፡፡መላእክታት ጻድቃንና ሰማዕታት ቢሆኑ በፍጹም አማላጅ ሆነ መካከለኛ ልሆኑ አይችሉም፡፡ከላይ እንደገለጽኩ የዕብራውያን ጻሐፍ ስናገር በዕብ 9፥15 ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ ፥የተጠሩት የዘላለም ርስት የተስፋ ቃል እንድቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፡፡ ይህንን ክፍል አስመለክቶ የጥንት ቤተክርስትያን አበው የነበረ ከ 349-407 ዓ.ም የኖረ ዮሐንስ አፈወርቅ ወይም ክሪሶስቶሞስ [20] ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መካከለኝነት ስናገር "መካከለኛ ማለት ምን ማለት ነው ?መካከለኛ መካከለኛ ለሆነለት ነገር ባለቤት ወይም ተጠቃም አይደለም፡፡ለምሳሌ መካከለኛ ለሚያገባ ሰው ሚስት ለማግባት አጋዥ ይሆናል እንጂ እርሱ የሚያገባ ሙሽራ አይደለም ፡፡በጌታም ዘንድ እንድህ ነው (የተሠዋው እጠቀም ብሎ አይደለም) ፡፡ወልድ ዋሕድ ጌታ በአባቱና በእኛ መካከል አስታራቂ ሆነ ፡፡ አብ በሰራነው ኃጢአት ፈርዶብን ነበር…ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጁ በእርሱና በእኛ መካከል አስታራቂ ሆነ፣እርሱንም ደስ አሰኘው፡፡"አሆ እርሱ ተጠቃሚ ሳሆን ጠቃሚ ሆነ፣መንግስተ ሰማያት እንዳንገባ የተከለከልነውን በመካከለኛነቱ መግባት ሆነልን አሜን፡፡

---

[13]ΠΡΟΣ ΤΙΜΟΘΕΟΝ Α΄ 2:5 Greek NT: Tischendorf 8th Edition

[15]NIV [17]1962 መጽሐፍ ቅዱስ [18]1997 የታተመው አ.መ.ት መጽሐፍ ቅዱስ [19]ግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስ

## ሊቀ ካህናት



ሊቀካህናት  የሚለው ከዕብራይስጥ ከሁለት  ኮሄን እና ጎዶውል ከምል ሁለት ጥምርት ቃላት የተገኘ ሲሆን አጫፍረን ስናነበው ኮይነ ጎዶውል ሲሆን ትርጉሙም የካህናት ስብስብ ሊቀንበር ወይም ዋና መሪ ማለት ነው፡፡የካህናት

አጀማመር ካዬን ፤ክህነት ሳይጀመር በፊት ሰዎች ራሳቸው ለእግዚአብሔር ይሠዉ ነበር፡፡ለአብነት ያክል

- **አቤል ዘፍ 4፡4**
- **ኖኅ ዘፍ 8፡20**
- **አብርሃም ዘፍ 15፡9-10፤22፡13**
- **ያዕቆብ ዘፍ 35፡3**

ሕግ ለእስራኤል ሕዝብ ስሰጥ ግን አሮንና ልጆቹ በክህነት እንዲያገለግሉ ተመረጡ፡፡ዘፍ 28፡1 ከአሮን ቤተሰብ ውጭ የሌዊ ዘሮች መሥዋዕት መሰዋት ባይችሉም በመቅደስ እንድያገለግሉ ተመርጠው ነበር ፡፡ዘኁ 3፡5-4 ሆኖም አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እራሱን ስገልጥ ግለሰቦቹ ለእግዚአብሔር ይሠዉ ነበር ፡፡

**ጌደኦን መሳ 6፡18-26**

ወደ አንተም እስክመለስ ድረስ፥ ቍርባኔንም አምጥቼ እስካቀርብልህ ድረስ፥ እባክህ፥ ከዚህ አትላወስ አለው። እርሱም። እስክትመለስ ድረስ እቆያለሁ አለ። ጌዴዎን ገባ የፍየሉንም ጠቦት የኢፍ መስፈሪያም ዱቄት የቂጣ እንጎቻ አዘጋጀ፤ ሥጋውን በሌማት አኖረ፥ መረቁንም በምንቸት ውስጥ አደረገ፥ ሁሉንም ይዞ በአድባሩ ዛፍ በታች አቀረበለት።የእግዚአብሔርም መልአክ። ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ ወስደህ በዚህ ድንጋይ ላይ አኑር፥ መረቁንም አፍስስ አለው። እንዲሁም አደረገ። የእግዚአብሔርም መልአክ በእጁ ያለውን የበትሩን ጫፍ ዘርግቶ ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ አስነካ፤ እሳትም ከድንጋዩ ውስጥ ወጥቶ ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ በላ። የእግዚአብሔርም መልአክ ከዓይኑ ተሰወረ። ጌዴዎንም የእግዚአብሔር መልአክ እንደ ሆነ አየ፤ ጌዴዎንም። አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ ወዮልኝ፤ የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና አለ። እግዚአብሔርም። ሰላም ለአንተ ይሁን፤ አትፍራ፤ አትሞትም አለው። ጌዴዎንም በዚያ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፥ ስሙንም። እግዚአብሔር ሰላም ብሎ ጠራው። እርሱም እስከ ዛሬ ድረስ ለአቢዔዝራውያን በምትሆነው በዖፍራ አለ።  እግዚአብሔርም በዚያ ሌሊት። የአባትህን በሬ፥ ሰባት ዓመት የሆነውን ሁለተኛውን በሬ፥ ውሰድ፥ የአባትህ የሆነውንም የበኣል መሠዊያ አፍርስ፥ በእርሱም ዙሪያ ያለውን የማምለኪያ ዐፀድ ቍረጥ፤በዚያም ኮረብታ አናት ላይ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር መሠዊያ አሳምረህ ሥራ ሁለተኛውንም በሬ ውሰድ፥ በዚያም በቈረጥኸው በማምለኪያ ዐፀዱ እንጨት ላይ የሚቃጠለውን መሥዋዕት አቅርብ አለው፡፡ኤልያስም ሕዝቡን ሁሉ። ወደ እኔ ቅረቡ አላቸው። ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡ። ፈርሶ የነበረውንም የእግዚአብሔርን መሠዊያ አበጀ።ኤልያስም። ስምህ እስራኤል ይሆናል የሚል የእግዚአብሔር ቃል እንደ ደረሰለት እንደ ያዕቆብ ልጆች ነገድ ቍጥር አሥራ ሁለቱን ድንጋዮች ወሰደ።  ከድንጋዮችም ለእግዚአብሔር ስም መሠዊያ ሠራ፤ በመሠዊያውም ዙሪያ ሁለት መስፈሪያ እህል የሚያዝ ጕድጓድ ቈፈረ።እንጨቱንም በተርታ አደረገ፥

ወይፈኑንም በብልት በብልቱ ቈረጠ፥ በእንጨቱም ላይ አኖረና። አራት ጋን ውኃ ሙሉ በሚቃጠለው መሥዋዕትና በእንጨቱ ላይ አፍስሱ አሉ። ደግሞም። ድገሙ አለ፤ እነርሱም ደገሙ። እርሱም። ሦስተኛ አድርጉ አለ፤ ሦስተኛም አደረጉ። ውኃውም በመሠዊያው ዙሪያ ፈሰሰ፤ ደግሞም ጕድጓዱን በውኃ ሞላው። መሥዋዕተ ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነቢዩ ኤልያስ ቀርቦ። አቤቱ፥ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፥ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ፥ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ፥ ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ። አንተ፥ አቤቱ፥ አምላክ እንደ ሆንህ፥ ልባቸውንም ደግሞ እንደ መለስህ ይህ ሕዝብ ያውቅ ዘንድ ስማኝ፥ አቤቱ፥ ስማኝ አለ። የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፥ የሚቃጠለውን መሥዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፥ በጕድጓዱም ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች።

**ኢዮብ ኢዮ 42፡8-9**

አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፥ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ፤ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፥ እኔም እንደስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ፤ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና። ቴማናዊውም ኤልፋዝ ሹሐዊውም በልዳዶስ ናዕማታዊውም ሶፋር ሄደው እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው አደረጉ እግዚአብሔርም የኢዮብን ፊት ተቀበለ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በመሆን እያገለገሉ የነበሩ ከሰው መካከል የተመረጡ ካህናት ነበሩ፡፡ዕብ 5፡1

**የእነዚህ ካህናት ዋና ዋና ሥራቸው፡-**

- ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኛሉ ፡፡ዘሌ 9፡15
- የሰዎችን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ያቀርባሉ፡፡ዕብ 8፡3
- የእግዚአብሔር መመርያዎችንና ሕግን ለሕዝቡ ያስተላልፋሉ፡፡ዘዳ 27፡9

ካህናት ወደ ቅድስት ገብቶ ሲያገለግሉ ፤ሊቀካህናት ግን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በአሜት አንድ ጊዜ በስርየት ቀን በመግባት አገልግሎት ይፈጽማሉ፡፡ዘሌ16፡2-3

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ይማልዳሉ፡፡

በብሉይ ኪዳን የሌዋውያን ሆነ የሊቀ ካህናት አገልግሎት ገደብ ነበረው÷ከ25 እስከ 30 ዓመት ባለው ዕድሜ በረዳትነት ÷ከ30-50 ዕድሜ በክህነትና በሊቀ ክህነት ያገለግሉ ነበር፡፡ዘኀ 4፡1-4

አንዳንድ ጊዜ ግን ከ20 ዓመት ጀምሮ ያገለገሉ አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡1ዜና 23፡24-27፤2ዜና 31፡17 ከ50 ዓመት በኃላ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ ከምደረግ አገለግሎት ቢወርዱም በማስተማርና ካህናትን በማዘጋጀት ያገለግሉ ነበር፡፡

# የኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ክህነት

በብሉይ ኪዳን ዘመን ኃጢአት የሰራ እስራኤላዊ ለኃጢአት መሥዋዕት የሚሆነውን ነውር የሌለበትን በግ ይዞ ወደ ካህናት የሄድና እጁን በበጉ ላይ ጭኖ ኃጢአቱን ከተናዘዘ በኃላ ካህኑ ስለ ኃጢአቱ ያስተሰርይለት ነበር ፡፡ዕብ 9፡6-10 በተለይ የብሉይ ኪዳን ሊቀካህነት ለአዲስ ኪዳን ሊቀካህን ለኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል ተምሳሌት እንደሆነ እንመለከታለን፡- የብሉይ ኪዳን ሊቀካህናት በደረታቸው አስራሁለት ዕንቁ ድንጋዮችን አስራሁለት የእስራኤል ነገዶችን በደልና ኃጢአታቸው ተሸክሞ በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ ፡፡እነዚህን እግዚአብሔር ቢመርጣቸውም ደካሞችና ማች ነበሩ ፡፡እነርሱ ራሳቸው ኃጢአተኞች ስለነበሩ፥ሕዝቡን ከዘላለም ፍርድ ኃጢአት ልያንጹ አልቻሉም ፤የአዲስ ኪዳን ሊቀካህን ግን ከኃጢአት በቀር እንደ እኛ ሰው የሆነ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር ፡፡አሮን የእስራኤልን በደል ተሸክሞ ወደ ቅድስት ቅዱሳን እንደምገባ ሁሉ ፥የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ የሆነው ክርስቶስ የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ተሸክሞ ወደ ቅድስት ቅዱሳን ገብቶአል ፡፡ኢሳ 53፥1-11

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ በኃላ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ይቆሙ ዘንድ ደም ይዞ ወደ ቅድስት ቅዱሳን የገባ የለም ፤ምክንያቱ እስከ ክርስቶስ ድረስ የነበሩ ሊቀ ካህናት ቊጥራቸውን ያበዛውና አንዱ በአንዱ እንድተካ ምክንያት የሆነው ሕያው ያለመሆናቸው ጉዳይ ነው ፡፡አንዱ ስሞት አንዱን ሲተካ ክርስቶስ ጋ ደረሰ ፥እርሱ ግን የማይሞትና ሞትን አሸንፎ ስለተነሣ ክህነቱ አልተተካም ፡ተተክ ስለሌለው ሊቀክህነቱ ዘላለማው ነው ፡፡ ዕብ 7፥23-25

በብሉይ ኪዳን የበግ ደም ተይዞ ወደ ቅድስት ቅዱሳን እንደምገባ ሁሉ ፥ኢየሱስ ክርስቶስ የበጎችንና የኮርማዎችን ደም ሳይሆን የገዛ ደሙን ይዞ ለእኛ በአብ ፊት ይታይ ዘንድ ወደ ሰማያዊት መቅደስ ገብቶአል ፡፡ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ስንቅርብ እርሱ እኛን እንደምረዳን በማመን ነው መቅረብ ያለብን ፡፡የኃጢአት ዋጋ ተከፍሏልና ፥ወደ እግዚአብሔር የምወስደው መንገዱ ለልጆቹ ክፍት ነው ፡፡ወደ ጸጋዊ ዙፋን በእምነት እንቀርባለን፤ምክንያቱም ልንወድቅ ስንል የሚደግፈን ጸጋ በዚህ ስፍራ እናገኛለን ፡፡አንዳንድ የሀገራችን ሰዎች አሻፈረኝ በማለት ሌላ መካከለኛ ያለቦታ ስሰነቅሩ ይታያሉ፤መካከለኛ አንድ ብቻ ከሆነ ለምን ሌሎችን ታዳብላላችሁ ስባል ፤የእነኝ መካከልኝነትና የኢየሱስ ይለያያል ብሎ አድስ ዶክትርን(አስተምህርት ) ሲቀርጹ ይስተዋላሉ፡፡ታዲያ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል አንድ መካከለኛ ብቻ ካለ ፤የእነኝ ሰዎች አድስ አስተምህሮት የተበጀላቸው በኢየሱስና በሰዎች መካከል መካከለኛ ሊሆኑ ነው? ኢየሱስ እራሱን አሳልፎ ለእኛ ቢሰጥም ወደ እርሱ ለመቅረብ ህልናችን አይፈቅድም ፥ስለማይፈቅድ መካከለኛ ያስፈልጋል ከተባለ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቁን ሕያው እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞት ሥራ ሕልናችሁን ያነጻ ይሁን ?ዕብ 9፥14 የኢየሱስ ደም ሕልናችን ያነጻናል እያለ እርሱ ጋ ለመቅረብ ሕልናችን ስለማይፈቅድ የሚለው አስተምህርት ከየት የመጣ ነው ? ሌላ መካከለኛ ወይም አማላጅ ማስገባት ኢየሱስ ያንተ ደም ብቻ ሊያነጻኝ አይችልም እንደማለት ነው ፡፡የፈሰሰው ደም ተራ ደም ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ የሆነና ፍጹም እንከን የሌለው

ነው፡፡ስለዚህ ንሰሐ ለመግባት ስንፈልግ በቀጥታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ወደ እግዚአብሐር መቅረብ እንችላለን ፡፡ዕብ 9÷28 የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት ልዩነቱ:-

| የብሉይ ኪዳን ሊቀካህን | የአዲስ ኪዳን ሊቀካህን |
|---|---|
| ሰው ብቻ ነበሩ ዕብ 5፡2 | አምላክ-ሰው ነበር ዮሐ 1፡1-2፤5፡20 |
| ክህነቱ ከሌዋዊያን ነገድ በመወለድና የአሮን ወገን በመሆን በዘር የሚገኝ ሲሆን ያለ መሃላ የተሰጠ ክህት ነው፡፡ ዕብ 7፡1 | ኢየሱስ ግን ከይሁዳ ነገድ የተወለደና ክህነቱ እንደ አሮን ሳይሆን እንደ መልከጼዴቅ የሆነ ከመሐላ ጋር የተሰጠ ክህነት ነው፡፡ዕብ 7፡11-12 |
| ሊቀካህኑ ኃጢአተኛ ሰለሆነ በእግዚአብሔር ፊት ስለእራሱም መሥዋዕትን ማቅረብ ይጠበቅበት ነበር ፡፡ዘሌ 11፡14፤ዕብ 5፡1 | ኢየሱስ ግን ኃጢአት የሌለበት ስለሆነ ለራሱ መሥዋዕት ማቅረብ አላስፈለገውም ፡፡ዕብ 7፡25 |
| ማች ነበሩ ፡፡ዕብ 7፡23 | ሕያውና ሞትን አሸንፎ የተነሳ ነው፡፡ዕብ 9፡12 |
| መሥዋዕቱ የእንስሳት ደም ነበር፡፡ዘሌ 16፡11-34 | መሥዋዕቱ እራሱ ነበር ፡፡ዕብ 9፡12 |
| መሥዋዕቱ ዕለት ዕለት ማለትም በተደጋጋም ይቀርብ ነበር ፡፡ ዕብ 7፡27፤10፡11 | አንድ ጊዜ ብቻ እራሱን ለመሥዋዕት አቀረበ፡፡ዕብ 7፡27፤ 9፡25 |
| በመሥዋዕቱ ፍጹም የሆነ ድነት አልተገኘም ፡፡ዕብ 9፡6-7 | መሥዋዕቱ ፍጹም የሆነ ድነት አስገኝቷል ፡፡ዕብ 7፡25 |
| በምድራዊ በተመቅደስ ነበር ያገለገሉ፡፡ዕብ 9፡6-7 | ሰማያዊ በሆነች ቤተመቅደስ ነው ያገለገለ፡፡ዕብ 8፡2 |

---

[20]ዮሐንስ አፈወርቂ በመጀመርያ የአንጾኪያ ፤ከዚያም በኃላ በቍስጥንጥንያ ጳጳስ በመሆን ቤተክርስቲያንን አገልግሎአል፡፡ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂ ከመሆኑም በላይ አስደናቂ የስብከትና ንግግር ስጦታ ስለ ነበረው አፈወርቂ የሚለው የቅጽል ስም ወጣለት ፡፡በፅርእ (ግሪክ) ቋንቋ ዮሐንስ ክሪሶስቶሞስ (John Chrysostom) ተባለ፡፡[21]ድርሳነ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቂ ፤ድር.16፡33-48, John crysostom, quoted in the catholic Encylopedia online page 133 ኤልያስ ነገ 18፡30-38

## ጠበቃ

ጠበቃ ማለት ባለጉዳይ ወክሎ በፍርድ ቤት የሚከራከር ፤የሚሟገት ፤ነገረ ፈጅ፤አፈ፤የነገር አባት ተማጓች፤ዶለተን ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ላመኑት ለልጆቹ ጠበቃ መሆኑንና በአብ ፊት መታየቱ ቃለ እግዚአብሔር ሳያወላዳ ይናገራል ።

> "ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።"1ኛ ዮሐንስ 2፥1
>
> *"My little children, these things write I unto you, that ye sin not. And if any man sin, we have an advocate with the Father, Jesus Christ the righteous:" 1 John 2:1 (KJV)*

"ማንም ኃጢያት ቢያደርግ" አባባሉ ክርስቲያኖችን ጨምሮ በሌሎችም ላይ ወደ ፊት ሊከሰት እንደሚችል ለማሳየት ሦስተኛ መደብ የተወሰነ ሁኔታን አመልካች ግስ የተነገረ አረፍተ ነገር ነው፡፡"በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን" በአሁኑ ጊዜ አድራጊ አመልካች ግስ የተነገረ አረፍተ ነገር ሲሆን ዮሐንስ አሁንም ስለ እኛ ቀጣይ የምልጃ ስራ በሰማያዊ ስፍራ በቆመልን ጠበቃ አማካኝነት እያቀረብልን መሆኑን፡፡

ቃሉ ስለእኛ ለመከራከር ወይም በውክልና ከጎናችን የቆመ የሕግ አዋቂን የምወክል ቃል ነው። ቃሉ ፖራ ከጎን እና ከሌዊ ተጠሪ ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል በምድር ጠበቃችን ሆኖ ስለሚላከው ስለመንፈስ ቅዱስ የተነገረ ነው፡(ዮሐንስ *14፡16፤25፤15፡26፤16፡7* ከዚህ ሌላ ኢየሱስን ለማመልከት ብቻ ተጠቅሷል *ዮሐንስ 14፡16፤ሮሜ 8፡34፤ዕብ 4፡14-16፤7፡25፤9፡24* ሐዋሪያው ጳውሎስ የክርስቶስ የምልጃ *ሥራ* ለማመልከት በሮሜ 8፡34፣በዚሁ መልክቱ ስለመንፈስ ቅዱስ አማላጅነት ሮሜ 8፡26 ተመሳሳይ ሀሳብ ለማስተላለፍ ተጠቅሚል፡፡ ሁለቱም አፍቃሪ አባታችን በእርሱ ምትክ የላካቸው ናቸው፡፡ [6]

በክርስቶስ ያመኑ አማኞች ኃጢአት እንዳያደርጉ የታዘዙ ስሆን፥ነገር ግን በሕይወት ዑደት ውስጥ እስከ አሉ ድረስ መሰናክሎችና ድካም (በኃጢአት መውደቅ)ይኖራል። ይህንን ሐዋርያዊ ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ስላወቀ ነው ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን ያለው። የኢየሱስ ጥብቅና ከደረስንበት ጽድቅ ወደ ኃላ እንዳናፈገፍግና ጠላት ስከሰን በደሙ መዋጀቱን መማገቱ ነው ።ኢየሱስ በደሙ ጠበቃችን ነው ። 1ኛ ዮሐንስ መልእክት 2፥1 ቃል እንዲህ ይላል፦ "ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።" በዚህ ጥቅስ ውስጥ ትልቁን ትርጉም የሚይዘው "ጠበቃ" ተብሎ የተተረጎመው "ፓራክሊቶስ" (Parakletos - παράκλητος) የሚለው ቃል ነው። ቃላዊ ትርጉም "ፓራ" (በአጠገብ) እና "ክሊቶስ" (የተጠራ) ከሚሉ ቃላት የተገኘ ሲሆን፣ ትርጉሙም

“በአጠገብ እንዲቆም የተጠራ” ማለት ነው። በጥንቱ ዓለም አንድ ሰው ፍርድ ቤት ሲቀርብ፣ በሕግ ዕውቀቱ እንዲረዳው ወይም ስለ መልካም ስነ-ምግባሩ ምስክር እንዲሆንለት በአጠገቡ የሚቆም “ረዳት” ወይም “ጠበቃ”

ማለት ነው። ዮሐንስ በወንጌሉ (ዮሐ 14:16) መንፈስ ቅዱስን “ሌላ አጽናኝ (ፓራክሊቶስ)” ሲል ጠርቶታል። እዚህ ጋር ደግሞ ክርስቶስን “ፓራክሊቶስ” ይለዋል። ይህም መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሆኖ እንደሚረዳን ሁሉ፣ ክርስቶስ ደግሞ በአብ ፊት ስለ እኛ እንደሚቆም ያሳያል። "ኃጢአትን እንዳታደርጉ" (Hina me hamartete)እዚህ ጋር ግሱ በ "Aorist Subjunctive" ተቀምጧል። ይህ የሚያሳየው ኃጢአት ድርጊት (Single act) መሆኑን ነው። ዓላማው አማኙ ፈጽሞ ኃጢአት እንዳይሠራ ነው። "ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ" (Ean tis hamarte)ይህ "Third-class condition" ነው። ትርጉሙም "ኃጢአት ብናደርግ እንኳ" የሚል ሲሆን፣ ኃጢአት ለአማኝ መደበኛ ኑሮ ሳይሆን ድንገት የሚወድቅበት አጋጣሚ መሆኑን ያሳያል። "አለን" (Echomen) ይህ ግስ በ "Present Indicative" (አሁን ያለ ሁኔታ) የተገለጸ ነው። ይህም ክርስቶስ ጠበቃነቱ ያልተቋረጠ እና ሁልጊዜም የሚሠራ መሆኑን ያረጋግጣል። "ኃጢአትን እንዳታደርጉ" በማለት አማኙ ወደ ቅድስና እንዲያዘነብል ያዛል። ይህ የጸጋን ትምህርት ለኃጢአት መሸፈኛ እንዳናደርገው የሚሰጥ ማስጠንቀቂያ ነው። ሰው ፍጹም አለመሆኑን ስለሚያውቅ "ቢያደርግ" በማለት የተስፋ በር ይከፍታል።መፍትሔው በእኛ ንስሐ ወይም በጽድቅ ሥራ ላይ ሳይሆን፣ በአብ ፊት ባለን "ጠበቃ" (ክርስቶስ) ላይ የተመሰረተ ነው።

1ዮሐ 2፥1 የሚያስተምረው ክርስቶስ በአብ ፊት ያለው ቦታ "ጻድቅ ጠበቃ" መሆኑን ነው። ይህ ጠበቃነቱ ደግሞ የፍጡራን ልመና ሳይሆን፣ በራሱ የባህርይ ጽድቅና በመስቀል ላይ በከፈለው ዋጋ ላይ የተመሰረተ መለኮታዊ ወካይነት (Advocacy) ነው። አማኙ ኃጢአት እንዳይሠራ ቢተጋም፣ ድንገት በሚወድቅበት ጊዜ ግን ወደ ተስፋ መቁረጥ ሳይሆን ወደ ጻድቁ ጠበቃው እንዲመለከት ያሳስባል።

---

*[5]አማረኛ መዝገበ ቃላት pg546 የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ 1993 ዐድስ የማረኛ መዝገብ ቃላት ከደስታ ተክለ ወልድ 1970 በአርትስት ማቴሚያ ቤት የታተሜ አአ pg536 advocate. One that pleads the cause of another. The term is commonly used to render Greek paraklētos G4156, found in 1 Jn. 2:1: “we have one who speaks to the Father in our defense”). John means that Christ is the legal advocate and intercessor with the Father when one falls into sin. The next verse shows that the basis of the intercession is Christ's propitiatory death for sin.This term occurs four other times in the NT (Jn. 14:16, 26; 15:26; 16:7),but in these passages it is a title given to the HOLY SPIRIT. In all four occurrences the KJV translates it “Comforter,” but recent English versions prefer renderings such as “Counselor” (NIV), “Helper” (NASB),“Advocate” (NRSV). ZONDERVAN ILLUSTRATED BIBLE DICTIONARY pg90 6]NIV - shared using Simple Bible*

## ከሞት በኃላ ምልጃ ወይም መማለድ የለም

መጽሐፍ ቅዱሳችን በማያሻማ ሁኔታ ከሞት በኃላ አንዱ ስለ አንዱ መጸለይና ከእግዝአብሔር ዘንድ ምህረትን መጠየቅ ሆነ መማለድ እንደለለ በግልጽ ያወራል፡፡በምድር ላይ ያሉ ፤በሰማይ ላሉ አካላት፤በሰማይ ላይ ያሉ መልአክት፤ ሰማታት ሆነ ቅዱሳን በምድር ላይ ላሉ አካላት መማለድ ሆነ ምህረትን መጠየቅ አይችሉም፡፡ኢየሱስ ክርስቶስ በሉቃስ 16፥19-31 ስናገር እንዲህ አለ፡-

> ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለጠጋ ሰው ነበረ፥ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር።አልዓዛርም የሚባል አንድ ድሀ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥ከባለጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር።ድሀውም ሞተ፥መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ባለጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ።እርሱም እየጮኸ፦አብርሃም አባት ሆይ፥ማረኝ፥በዚህነ በልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ።አብርሃም ግን ፦ልጄ ሆይ፥አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እን ዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።እርሱም፦እን ኪያስ፥አባት ሆይ ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤አምስት ወንድሞች አሉኝና፤እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።አብርሃም ግን ፦ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤እነርሱን ይስሙ አለው። እርሱም፦አይደለም፥አብርሃም አባት ሆይ፥ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ።ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ፥ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነ ሣ አያምኑም አለው።

ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው አብርሃም የሁሉ አባት እንደሆነ ደግሞ ገነት የርሱ እቅፍ እንደሆነች እንረዳለን ፡፡ነገር ግን ለማንም ከእግዝአብሄር ምህረትን መለመን አልያም መማለድ እንደማይችልና ከስኦል አውጥቶ ወደ ገነት ማስገባት እንደማይችል በግልጽ እንረዳለን፡፡ስለዚህ ነው የሰማይ አካላት በምድር አካላት ላይ ተጽህኖ ማምጣት የማይችሉ፡፡ እንኳንስ የምድር አካል በምድር አካል ላይ በጸሎትና በምልጃ ተጽኖ ማሳደር ብችሉም የሰማይ አካል በምድርም ሆነ በሰማይ አካል ላይ ተጽን ማሳደር አይችሉም፤ ይህ ስባል መማለድ ሆነ መለመን እንደማይችሉ ለመግለጽ ነው፡፡ መላእክት ቢሆኑም የኢየሱስ እናት ማርያም ቢትሆንም መጸለይ ሆነ መማለድ በሰማይ አይችሉም ፡፡እንዲያውም ክፍሉ በኃጢአተኞችና በጻድቃን መካከል አንዱ ወደ አንዱ እንዳያልፍ ትልቅ ድንበር እንዳለ ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ ይደግፋል፡፡

## በፍጡራን ስም መማጸን አግባብነት አለውን?

ስም ማለት የአንድ ነገር መጠርያ ሲሆን ፤ስም የባለበቱን ማንነትና ስልጣንን ይወክላል፡፡ለምሳሌ ኢየሱስ በአባቴ ስም መጣሁ ስል በአባቴ ስልጣን መጣሁ ማለቱ ነበር፡፡ዮሐ 5፡43

ከሰማይ በታች ሌላ ስም ተሰፋ አድርጎ መጥራት የተከፈለልንን የደም ክፍያ ዋጋ ማሳጣትና ኃጢአትን ማስተሰረይ የሚችለውን ስም እንደማጥላላት ይቆጠራል፡፡1 ዮሐ 2፡12፤ሐዋ 10፡43፤ዮሐ 20፡30 ልመሰገንና ልጠራ የሚገባ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ ነው፤ለድነት ሆነ ለመማጸንም ከሰማይ በታች ሌላ ስም የለም፡፡ማንኛውም ነገር ማድረግ የሚገባን በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ መሆን እንዳለበት መጽሀፍ ቅዱስ መመርያ ይሰጠናል፡፡ቆላ 3፡17 በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ዝና አላቸው ከምንላቸው ውስጥ እስጥፋኖስና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስሆኑ፤እስጥፋኖስ የሰማዕትነት በር ከፋች[12] ቢሆንም ሐዋርያቱ ለእስጥፋኖስ ገድልና ዜማ ደርሰው፡ስንኝ ቋጥረው ፡በገና ደርድረው አልዘመሩለትም ቅኔን አልተቀኙለትም፤በስሙም አልተማጸኑም ፤የአክብሮት ስግደት አልሰገዱም፡፡እንደ እስጥፋኖስ ያለ ሰው የለም ፤መዘከር ብቻል ኖሮ ለእስጥፋኖስ መዘከር ነበር ፡ለእርሱ ያልተዘከረ ለተክልያማኖት ለዑራኤልና ለሩፋኤል መዝከር ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ ሳይሆን የኢጋንንት አሰራርና የባህድ አምልኮ ነው፡፡የእስጥፋኖስ አገልግሎት ይህንን ይመስል ነበር፡-

- መንፈስ ቅዱስ የሞላበት ሐዋ 6፡5
- ጸጋና ኃይል ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድቅና ታላቅ ምልክት ያደርግ
- ፊቱ እንደ መልአክት የሆነ ሰው ነበር ቁጥር 15
- ኢየሱስን በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ያየ ሰው ነበር ሐዋ 7፡55

## ጸሐይ የተጎጸፈች ሴት ማርያም ናት?

*ታላቅ ምልክት በሰማይ ታዪ ፤ፀሐይ ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት በራስዋም ላይ የአስራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንድት ሴት ነበረች ፤እርሶዋም ፀንሳ ነበረች፤በምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች፡፡ራእ12፡1-2*

ከቁ 1 እንደምንረዳ ሴትቷ እስራኤል ናት፡፡ይች ሴት እስራኤል እንጂ ቤተክርስትያን ወይም የጌታ እናት ማርያም አይደለችም፡፡

❖ **እስራኤል መሆኗን**

1.<u>አስራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት</u> ይህ አስራ ሁለት ነገድ ያመለክታል፡፡

2. እስራኤል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን እንዳገባች ሴት ሆና ከእግዚአብሔር ባደረገችው ቃልኪዳን ትታወቃለች፡፡ ኢሳ 54፡4-6፤ኤር 3፡11-14 ሆሴ 2፡16-22 1ቆሮ 11፡3

3.<u>በምጥ መውለድ</u> በመጽሐፍ ቅዱሳችን በመጨረሻ ዘመን በምጥ የምወለዱ ሕዝቦች በመባል የተጠቀሱት አይሁድ ብቻ ናቸው፡፡ራእ 12፡2-5፤ማቴ 24፡8፤ማር 13፡8፤ኢሳ 66፡7-8፤ኤር 30፡6-8

4. ሴትቱን ዘንዶ አሳድዳቷል እንዲሁም እስራኤላውያን በመጨረሻ ዘመን ከሚያሳድዷቸው ከጠላቶቻቸው ፊት ወደ ምድረ በዳ እንደምሸሹ በእግዚአብሔር ቃል በተለያየ ሥፍራ ተጽፎአል፡

❖ **ማርያም አለመሆና**

1. 1260 ቀናት ማርያም አልተሰደደችም
2. በምጥ ተሸግራ መጮኻን መጽሐፍ ቅዱስ አያውስም
3. አስራ ሁለት ከዋክብት የሆነላት አክሊል አላደረገችም ደግሞ ጨረቃን ከእግሮቻ በታች አልረገጠችም፡፡

❖ **ቤተክርስትያን ያለመሆና**

ቤተክርስቲያን ራይ ምዕራፍ ሶስት ላይ ተነጥቃለች ድጋም ከተነጠቀች በኃላ ከየት ትመጣለች ?

## የጥንት ቤተክርስቲያን አበዎች ስለኢየሱስ አማላጅነት ምስክርነት

የጥንት ቤተክርስቲያን አበዎች (Church Fathers) ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት እና ሊቀ ካህንነት በስፋትና በጥልቀት አስተምረዋል። የእነሱ ትምህርት በዋናነት በዕብራውያን መልእክት (በተለይ ምዕራፍ 7-9) እና በ1ኛ ዮሐንስ መልእክት 2:1 ላይ የተመሠረተ ነው። ለእነሱ የክርስቶስ አማላጅነት የደካማነት ምልክት ሳይሆን፣ የድል አድራጊነቱ እና ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያለው አንድነት መገለጫ ነው። እርሱ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕቱን አቅራቢ (ካህን) በመሆን በሰማያዊው መቅደስ ስለ እኛ ይማልዳል። ከዚህ በታች በጥንት ቤተክርስቲያን ታዋቂ ከሆኑት አባቶች መካከል አንዳንዶቹ ስለዚሁ ርዕስ የሰጡትን ምስክርነት አቅርቤልሃለሁ:-

1. ቅዱስ ክሌመንት ዘሮም (St. Clement of Rome) - 1ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ይህ አባት ከሐዋርያት ቀጥሎ ከነበሩት የመጀመሪያዎቹ አባቶች (Apostolic Fathers) አንዱ ነው። ስለ ክርስቶስ አማላጅነት ሲናገር:- "የተወደዳችሁ ሆይ፣ የመዳናችን መንገድ ይህ ነው፤ እርሱም የመሥዋዕታችን ሊቀ ካህን፣ የድካማችን ረዳትና አማላጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።"[22]

2. ቅዱስ አምብሮስ (St. Ambrose of Milan) - 4ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ቅዱስ አምብሮስ የክርስቶስ አማላጅነት ከስቅለቱ እና ከትንሣኤው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው ያስተምራል። እርሱ ስለ እኛ ለአብ የሚያቀርበው የቆሰለውን አካሉን (የመሥዋዕቱን ምልክት) ነው ይላል

"እርሱ [ክርስቶስ] በደካማነታችን ምክንያት [ሥጋን በመልበሱ] ይማልዳል፤ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ልጅነቱ ኃይል አለው። [...] እርሱ ስለ እኛ ይማልዳል ስንል፣ ለአብ የቆሰለውን አካሉን፣ ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ እንደሚያሳይ አድርገህ እወቅ።"[23]

3. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (St. John Chrysostom) - 4ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ይህ ታላቅ አባት የዕብራውያን መልእክትን በተረጎመበት ድርሳኑ ላይ፣ የክርስቶስ አማላጅነት ዘላለማዊ መሆኑን እና እርሱ ሁልጊዜ በፊቱ ቆሞ እንደሚለምን ሳይሆን፣ በመሥዋዕትነቱ ውጤት ሁልጊዜ በፊቱ እንደሚታይ ያብራራል። "'ስለ እነርሱ ሊያማልድ ሁልጊዜ በሕይወት ይኖራልና' (ዕብ. 7:25)። [...] አማላጅነቱ ምንድነው? እንደ ተራ ተማላጅ በፊቱ ይቆማል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ስለ እኛ መሥዋዕት ሆኖ ራሱን ስለሚያቀርብ፣ ይህ መሥዋዕትነቱ ሁልጊዜ በፊቱ ስላለ፣ ያ አማላጅነት ነው።"[24]

4. ቅዱስ አውግስጢኖስ (St. Augustine of Hippo) - 4ኛው/5ኛው ክፍለ ዘመን የኖረ አውግስጢኖስ ክርስቶስ እንደ አምላክነቱ ጸሎታችንን እንደሚሰማ፣ እንደ ሰውነቱ (እንደ ሊቀ ካህንነቱ) ደግሞ ስለ እኛ እንደሚጸልይ (እንደሚማልድ) ያስተምራል። "እርሱ [ክርስቶስ] ስለ እኛ ይጸልያል (ይማልዳል)፣ በእኛ ውስጥ ይጸልያል፣ እኛም ወደ እርሱ እንጸልያለን። ስለ እኛ የሚጸልየው ሊቀ ካህናችን በመሆኑ ነው፤ በእኛ ውስጥ የሚጸልየው ራሳችን በመሆኑ ነው፤ ወደ እርሱ የምንጸልየው አምላካችን በመሆኑ ነው።"[25]

5. ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ (St. Cyril of Alexandria) - 5ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ

የቤተክርስቲያን ዓምድ የሆነ አባት፣ የክርስቶስ አማላጅነት ለአብ ያለውን ፍጹም መታዘዝ እና የሰውን ልጅ ወደ አምላክ የመመለስ ሥራውን እንደሚገልጽ ይናገራል። "እርሱ የፈጠረውንና [በኃጢአት] የወደቀውን የሰውን ልጅ በራሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር አብ ይመልሳል። ይህንንም የሚያደርገው ለአብ የመታዘዝን መሥዋዕት በማቅረብ ነው። [...] በራሱ በኩል እኛን ለአብ ያስታርቃል፤ ይህ ነው አማላጅነቱ።"[26] የጥንት አባቶች ትምህርት በሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ያተኩራል፡ ክርስቶስ ብቸኛው እና ፍጹሙ አማላጅ ነው፡ እርሱ ራሱ አምላክና ሰው በመሆኑ እግዚአብሔርንና ሰውን ያስታረቀ ብቸኛ መካከለኛ ነው። አማላጅነቱ የመሥዋዕትነቱ ውጤት ነው፡ እርሱ አሁንም በሰማይ በፊቱ የሚማልደው በምድር ላይ የፈጸመውን ቤዛነትና ፍጹም መሥዋዕትነት ለአብ እያሳየ ነው።

6. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዝናዙ (Gregory of Nazianzus): "እርሱ [ክርስቶስ] አሁንም እንደ ሰው ይማልዳል... እኛን ለማዳን በለበሰው ሥጋ አማካኝነት ለአብ ይማልዳል።" (Oration 30.14)

---

*[5]አማረኛ መዝገበ ቃላት pg546 የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ 1993 ዐድስ የማረኛ መዝገበ ቃላት ከደስታ ተክለ ወልድ 1970 በአርትስት ማቴሚያ ቤት የታተሜ አአ pg536 advocate. One that pleads the cause of another. The term is commonly used to render Greek paraklētos G4156, found in 1 Jn. 2:1: "we have one who speaks to the Father in our defense"). John means that Christ is the legal advocate and intercessor with the Father when one falls into sin. The next verse shows that the basis of the intercession is Christ's propitiatory death for sin.This term occurs four other times in the NT (Jn. 14:16, 26; 15:26; 16:7),but in these passages it is a title given to the HOLY SPIRIT. In all four occurrences the KJV translates it "Comforter," but recent English versions prefer renderings such as "Counselor" (NIV), "Helper" (NASB),"Advocate" (NRSV). ZONDERVAN ILLUSTRATED BIBLE DICTIONARY pg90 6]NIV - shared using Simple Bible*

*[22] First Epistle to the Corinthians (፩ኛ ክሌመንት)፣ Chapter 36። (ይህ መጽሐፍ በተለያዩ የአበዎች ስብስቦች ውስጥ ይገኛል፣ ለምሳሌ፡ The Ante-Nicene Fathers, Vol. 1) [23]De Fide (On the Christian Faith), Book V, Chapter 14, Section 180-182። (ምንጭ፡ Nicene and Post-Nicene Fathers, Second Series, Vol. 10) [25]Expositions on the Psalms, Psalm 86 (85 በላቲን ቁጠራ)፣ Section 1። (ምንጭ፡ Nicene and Post-Nicene Fathers, First Series, Vol. 8) [26]Commentary on John, Book XI (የሐንስ 17ን በተረጎመበት ክፍል)። (ምንጭ፡ Cyril of Alexandria, Commentary on John, Vol. II, tr. P.E. Pusey)*

*ምንጭ፡ Homilies on Hebrews, Homily 13 (ዕብ. 7:25ን በተረጎመበት ክፍል)። (ምንጭ፡ Nicene and Post-Nicene Fathers, First Series, Vol.*

## መላእክትና ቅዱሳን መማለድ የማይችሉባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች

ብዙዎች ቅዱሳንና መላእክት ይማልዳሉ ብለው የሚያምኑት ለክርስቶስ ያለንን ክብር ዝቅ ለማድረግ ባይሆንም፤ ሳያውቁት ግን የክርስቶስን ፍጹም አዳኝነትና ብቸኛ መካከለኛነት ይጋፋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ፍጡራን (መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን) መማለድ እንደማይችሉ የሚያሳዩባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው:-

### 1. የባሕርይ ውስንነት (Limited Nature)

መማለድ ወይም የሰውን ጸሎት ሰምቶ ለእግዚአብሔር ማቅረብ "ሁሉን ማወቅን" (Omniscience) ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱስ "ልባቸውን የምታውቅ አንተ ብቻ ነህና" (2ኛ ዜና 6፡30)ይላል ። መላእክትና ቅዱሳን ፍጡራን ናቸው። ፍጡር ደግሞ በአንድ ጊዜ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሚያቀርቡትን የልብ ሐሳብና የውስጥ ጸሎት የመስማት መለኮታዊ ባሕርይ የለውም። የሰውን ልብ መመርመር የሚችለው ፈጣሪ ብቻ ነው። ስለዚህ ያልሰሙትን ጸሎት ማቅረብ አይችሉም።

### 2. የቤዛነት (የመሥዋዕት) እጥረት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አማላጅነት ከመሥዋዕት ጋር የተያያዘ ነው።

"ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ... መካከለኛው አንድ ነው" (1ኛ ጢሞ 2፡5-6)። ክርስቶስ የሚማልደው ስለ እኛ የፈሰሰ ደም ስላለው ነው። መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን ግን ስለ እኛ የፈሰሰ ደም የላቸውም፤ ቤዛም አልሆኑልንም። ቤዛ ያልሆነ አማላጅ (መካከለኛ) ሊሆን አይችልም። የራሳቸው ደም ሳይፈስ "እማልዳለሁ" ማለት የክርስቶስን ደም ዋጋ ማቃለል ይሆናል።

### 3. መላእክትና ቅዱሳን "አገልጋዮች" እንጂ "አማላጆች" አይደሉም

መጽሐፍ ቅዱስ የመላእክትን ተግባር ሲገልጽ አገልጋይነታቸውን እንጂ አማላጅነታቸውን አይደለም። "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገልገል የሚላኩ የሚያገለግሉ መናፍስት አይደሉምን?" (ዕብ 1፡14)። መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ እኛ መልእክትና እርዳታ ይዘው የሚመጡ "አገልጋዮች" ናቸው እንጂ ከእኛ ወደ እግዚአብሔር የሚወስዱ "አማላጆች" አይደሉም። መላእክት በመሰላሉ (በክርስቶስ) ላይ የሚወጡና የሚወርዱ አገልጋዮች እንጂ እነርሱ ራሳቸው መሰላሉ አይደሉም።

### 4. ሙታን በምድር ያለውን ነገር አያውቁም

በአካል ከዚህ ዓለም የተለዩ ቅዱሳን በምድር ስላለው ነገር ያላቸው እውቀት ውስን ነው።"ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና፤ ሙታን ግን አንዳች አያውቁም... ከፀሐይ በታችም በሚደረገው ነገር ለዘላለም ድርሻ የላቸውም"(መክ 9፡ 5-6)።

ይህ ጥቅስ የሚያሳየው በምድር ባለው የሰው ልጆች እንቅስቃሴና ጸሎት ውስጥ ሙታን ጣልቃ የመግባት ወይም የመስማት ድርሻ እንደሌላቸው ነው። ቅዱሳን በክብር ቢኖሩም፣ ሥራቸው እግዚአብሔርን ማመስገን እንጂ የሰውን ጸሎት "ፖስታ ቤት" ሆነው ማመላለስ አይደለም።

### 5. ወደ ጸጋው ዙፋን በቀጥታ የመቅረብ መብት

ሌላ አማላጅ መፈለግ ክርስቶስ ወደ አባቱ የከፈተልንን በር እንደመዝጋት ይቆጠራል። "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል... ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ" (ዕብ 4፡16)። ክርስቶስ መጋረጃውን ቀድዶ በቀጥታ ወደ አብ እንድንገባ መብት ሰጥቶናል። ንጉሡ "በሩ ክፍት ነው ግባ" እያለን፣ እኛ ደጅ ጠኚዎችን "አማልዱኝ" ማለታችን በንጉሡ (በክርስቶስ) ተስፋ አለመተማመናችንን ያሳያል።

## ጽዮን ድንግል ማርያም ናት ወይስ ሌላ?

ጽዮን የሚለው ይህ ስም በብሉይ ኪዳን ለመጀመርያ ጊዜ የተጠቀሰው በ 2ኛሳሙ 5፡7 ላይ ነው፡፡በመጀመርያ ይህ ስም የኢያቡሳውያን ምሽግ የምገኝበት ከተማ የደቡብ ጫፍ ኮረብታ ተሰጥቶ የነበረ መጠርያ ይመስላል፡፡ከተማይታ ከሰለሞን ዘመን መንግስት ጀምሮ እየተስፋፋች ስትሄድ ይህ ስም የመላዋ ከተማ መጠርያ ሆነ፡፡በዚ ከተማ የምገኙ ዘጎች ወይም ነዋሮዎች «የጽዮን ሴት ልጅ ተብሎ ተጠርቶአል፡፡ኢሳ 1፡8

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ጽዮን ለማርያም የተሰጠ ለላኛው ስም ነውይላሉ፡፡

እነርሱ ከምጠቅሱት ክፍሎች እስክ አብረን እንደ ሐረጉና ዐውዱ እንቃኛለን፡፡

> *1ነገ 8፡1-2 ፡-ሰለሞንም የእግዝአብሔር ቃልኪዳኑ ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን ያወጡ ዘንድ የእስራኤልን ሽማግለወችንና የነገድ አለቆችን ሁሉ የእስራኤልን ልጆች የአባቶቻቸውን ቤቶች ፡መሳፍት ፡ንጉሱ ሰለሞን ወዳለበት ወደ እየሩሳሌም ሰበሰባቸው፡፡*

በዚ ክፍል ውስጥ የቃልክዳኑን ታቦት እንመለከታለን፡፡ህዝቡም በጽዮን ከተማ ታቦቱን ይዞ ለማምጣት ስሰባሰብ እንመለከታለን፡፡ጽዮን የተባለች ቦታ እንጂ ድንግል ማርያም ወይም ታቦቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ከድንግል ማርያም ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም፡፡ለማርያም የተጋነነ ሥፍራ ከሰጡ ውጭ ድንግል ማርያም ጽዮን ያለመሆኗ ንጉስ ሰለሞን የቃልክዳኑን ታቦት ጽዮን ከተባለበት ቦታ እንድያወጡ የእስራኤልን አለቆች፡መሳፍንትን እና ካህናትን መሰብሰቡን እንመለከታለን፡፡

ኢሳ 8፡18«እነሆ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች በጽዮን ተራራ ከምኖረው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ለእስራኤል ምልክትና ድንቅ ነን፡፡

በዚህ ክፍል ውስጥ ነብዩ ኢሳያስ እግዚአብሔር የሰጠው ልጆች በጽዮን ተራራ ከምኖረው እግዚአብሔር ዘንድ ምልክትና ተአምራት እንደሆኑ  ስያስረዳ እንመለከታለን ወይም እግዚአብሔር በኢሳያስ አማካይነት እንደገናም ኢሳያስና ልጆቹ የገለጹትን በድንቅና ምልክት የተደገፈውን የእግዚአብሔርን ቃል  በመከተል ብቻ በጽዮ ተራራ በኢየሩሳለም ለምኖሩ የንጋት ብርሃን እንምወጣ ይናገራል፡፡አሁን እየተመለከተን ያለነው ክፍል ጽዮን በኢየሩሳለም ውስጥ የምገኝ ግዙፍና ታላቅ ተራራ መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም ድንግል ማርያም ወይም የቃልኪዳኑ ታቦት አይደሉም፡፡ ኮረብ የእግዚአብሔርን ተራራ ተብሎ ተጠርቷል፤የእግዚአብሔርን ተራራ ተብሎ የተጠራ ሁሉ ለድንግል ማርያም አይሆንም እርስዋም ተራራ አይደለችም፡፡

*ኢሳ 24፡23 የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን በጽዮን ተራራና በኢየሩሳለም በሽማግለዎች ፊት በክብሩ ይነግሣል፡፡*

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር በእርግጥ በጽዮን ተራራ በኢየሩሳለም እንደምነግስ የተገለጠበት ክፍል ነው፡፡ጽዮን የዳዊትና ዘሩ ሁሉ መናገሻ ከተማ ናት፡፡በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል በእስራኤልም(በያዕቆብ) ቤት ለዘላለም ይነግሣል መንግስቱ መጨረሻ የለውም፡፡ሉቃ 1፡3 ተብሎአል፡፡ስለዚህ እግዚአብሔርን በእየሩሳለም (ጽዮን) ከተማ በያዕቆብ ቤት ላይ የሚነግሥ ተባለ እንጂ በድንግል ማርያም ይነግሳል ለማለት የተጻፈ አይደለም-፡ ጽዮን ማርያም ናት የሚለው ሀሳብ ለክፍሉ ባዕድ ሀሳብ ነው፡፡እግዚአብሔርን በሁሉም ላይ ንጉስ ነው፡፡

ኢሳ 1፡8 በዚህ ክፍል ደግሞ በክፉ ሰዎች እጅ የወደቀችና  የተዋረደች ሴት ልጅ እንዳላት ሆና ቀርባለች ፡-የጽዮን ሴት ልጅም  የተከበበች ሆና ቀርባለች  በዚህ ክፍል ጽዮን ድንግል ማርያም ናት ካለን የድንግል ማርያም ሴት ልጅ ማናት ድንግል ማርያም  በወይን ቦታ እንዳለ ዳስና በአትክልት  እንዳለ ጎጆ እንደተከበበችም  ከተማ ሴትን ወልዳለችን ለድንግል ማርያም አንድ ሴት ልጅ ካለቻትስ የድንግልና ጉዳይ  አያነጋግርም ኦርቶዶክስያውያን  ማርያም ለዘላለም ድንግል ናት ስለምሉ በዚ ክፍል የተጠቀሰች ጽዮን ማርያም ከሆነች ለዘላለም ድንግልና የላትም ማለት ነው፡፡በመሰረቱ የማርያም ድንግልና ዘላለማው አይደለም፡፡

ኢየሱስን በድንግልና ብትወልድም ከኢየሱስ ውጭ እንደ ወለደች አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይጠቁማል፡፡ ማቴ 12፡46-47 ሉቃ 8፡19 በዚህ ክፍል ኢየሱስ እንዲህ ያለ መልስ መስጠቱ፡ከስጋ ዘመዶች ጋር ያለውን ግንኙነት ለመቀበል ፈልጎ ሳይሆን፡በእርሱ ካመኑት ጋረ ያለውን መንፈሳዊ ግንኙነት የላቀ መሆኑን በአጽኖት ለማየት ነው፡፡ዮሐ 7፡5፤ሰሉቃ 8፡21

## የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ብዙ ጊዜ የሚያነሱ ጥያቄዎች

**ጥያቄ 1፦** ኢየሱስ አማላጅ ከሆነ (ሮሜ 8፡4፤ዕብ 7፡25) መንፈስ ቅዱስም ደግሞ አማላጅ ከሆነ (ሮሜ 8፡ 26) እግዘአብሔር አብ አማላጅ ነው ከታባለ (ኤር 7፡25) ታዲያ ሦስቱ ወደ ማን ይማልዳሉ?

**መልስ፦**

### የመንፈስ ቅዱስ አማላጅነት

ይህ ጥያቄ ስንመለከት አውዱን ያላገናዘበ ጥያቄ ነው፤በመጀመርያ በእውኑ መንፈስ ቅዱስ ይማልዳልን ? መልሱ አሆ የሚል ነው፤መንፈስ ቅዱስ ይማልዳል ስንል እግዝአብሔር ይለምናል ማለታችን አይደለም፡፡የመንፈስ ቅዱስ ምልጃ ስለ ኃጢአት ስርየት ሳይሆን እንድንጸልይ መርዳቱ ነው፡፡ይማልድልናል የሚለው ቃል እኛ የሚንጸልየውን ወይም የሚንቃትተውን እንደት እንደሚንሆን ስለማናውቅ በቅድምያ(ቀደም ብሎ) የሚንጸልይበትን ነገር ያስታውቀናል የሚል ትርጉም አለው፡፡ እኛ ብዙ ጊዜ ለራሳችንም ሆነ ለሌሎችም መጸለይ የሚገባንን አናውቅም፤መንፈስ ቅዱስ ግን የሰውን ጥልቅ ምስጥር የሆነውን ስለሚያውቅ በእኛ ውስጥ በመሆን እንድንጸልይ(እንድንማልድ) ይጠይቀናል፡፡ነገ ምን እንደምደርስብን አናውቅም እርሱ ግን ቀደም ብሎ የሚመጣውን ነገር በማሳየት ለጸሎት ያነሳሳናል ማለት ነው፡፡ስለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ በጎ ፍቃዱ መፈለግን ማድረግን በእናንተ ውስጥ የሚሰራ እግዚአብሔር ነው የሚለው፡፡

### የእግዚአብሔር አብ አማላጅነት

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ስፍራ እግዚአብሔር አብ አማላጅ ነው የሚል የለም ይልቁንም ይማልዳል ይላል እንጅ፡፡ለዚህም ብዙ ጊዜ ኦርቶዶክሳዊያን የምጠቅሱ ክፍል ኤር 7፡25 ስሆን ክፍሉ እንድ ይላል፦

> አባቶቻችሁን ከግብጽ ምድረ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በየቀኑ እየማለድሁ አገልጋዮቼን ነቢያትን ላክሁባቸው፡፡

ከክፍሉ የሚንረዳ ኦርቶዶክሳዊያን እግዚአብሔር አብ እየማለደ ነው ይበሉ እንጅ ክፍሉ በፍጹምእግዚአብሔር አብ አማላጅ ነው አይልም፡፡እየማለድሁ (Rising early) በጥዋት ወይም ቅድምያ በመነሳት የሚል ሀሳብ ያለው እንጂ መለመን የሚል ሀሳብ የለውም፡፡እስራኤል በበደላቸው ምክንያት እንዳይጠፉ ቀደም ቢለው ወይም በመማለድ (በመቅደም) በፍርድ እንዳይጠፉ ነቢያትንና አገልጋዮችን መላኩን እንጅ ፤እግዚአብሔር አብ አማላጅ (የሚለምን) ነው ማለቱ አይደለም፡፡

## የኢየሱስ አማላጅነት

ኢየሱስ የሚማልደው ከኃጢአት አንጻር ነው

**ጥያቄ 2፡- በሉቃ 1፡19 ላይ መልአኩ ገብርኤል"እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ" ብሎ መናገሩ አማላጅነቱን አያመለክትምን? መቆም ማለት መማለድ ማለት ከሆነ ለምን በመላእክት አማላጅነት አታምኑም?**

**መልስ፡-**

ክፍሉ ልብ ብለን ካየን መልአኩ ገብርኤል አማላጅ መሆኑን አያመለክትም፤መቆም ማለት እንደ ዐውዱ ብለያይም በዚህ ዐውድ ውስጥ ግን እግዚአብሔር ጋ መገኘት ማለት ስሆን ለተሰጠው አላማ ሳይታክት ማገልገል ወይም ለተላከ ተልዕኮ መበረታታትና ዝግጁ መሆን ማለትም ጭምር ነው እንጅ መማለድ ማለት አይደለም፡፡መልአኩ ገብርኤል የሚላክና በትጋት እግዚአብሔርን የሚያገለግል አልያም ከእግዚአብሔር አፍ ትእዛዝ ስወጣ ለመላክ ዝግጁ ነኝ ማለቱ ነው እንጅ ፤ለሰው ልጅ ኃጢአት የሚማልድ ነኝ ማለቱ አይደለም፡፡መቆም የሚለው የግርኩ ቃል παρί στη ἐν ώπι ο/ ፓርስታንኦ እንኦፐኦን/ **stand in the presence of God**[30] በእግዚአብሔር ፊት መገኘት ማለት ነው፡፡ለምሳሌ በራእ 12፡4 ዘንዶውም ሴትቱ በወለደች ጊዜ ሕጻንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ በዚህ ክፍል ቆመ[31] የተባለው የዘንዶው አቋም ወይም የመዋጡ ተልዕኮን በትክክል ለመወጣት መጽናቱን አመልካች ስሆን ሴትቱ ጋ ለመዋጥ ተገኝ የሚል ፍቺ አለው እንጂ ለመማለድ መቆሙን አያመለክትም፡፡ ቆመ በሚለው ሥፍራ ሁሉ ማለደ ብለን ለመተረጎም መዳዳት የለብንም፡፡

---

[3] KJV"And the angel answering said unto him, I am Gabriel, that stand in the presence of God; and am sent to speak unto thee, and to shew thee these glad tidings. "[3] stand by/present/yield/with

**ጥያቄ 3፦- የእሴይ በትር ማርያም አይደለችምን?**

**መልስ፦-**

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች አብዛኛዎቹ መምህራን የእሴይ በትር ማርያም ናት ይላሉ፤ ምክንያቱም ከማርያም ስለተወለደ ብሎ ስያስተምሩና ስከራከሩ ይደመጣሉ፡፡ እስክ በጥሞና መንፈስ ሆነን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት እንቃኝ፡፡

"ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል"

"ከእሴይ ግንድ ቁጥቋጥ ይወጣል[3]"ኢሳ 11፡1

ልብ ማድረግ የሚገባን ነገር ብኖር በትሩ ከግንድ ነው ወይስ ግንዱ ከበትር ነው የሚወጣ፤እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በትሩ (ቁጥቋጦ) ከግንድ ይወጣል እንጂ ግንድ ከበትር አይወጣም፡፡እንደ ኦርቶዶክሳውያን መምህራን በትር ማርያም ከሆነችና ግንዱ ኢየሱስ ከሆነ ማርያም ከኢየሱስ ማህፀን ተወለደች ወደ ማለቱ አይመራንም ?፡፡ በትር የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣንና ንግስናን ነው፡፡ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል ስል ከእሴይ ቤት የምሾም ንጉስ ይነሳል ማለቱ ነው፡፡የእሴይ በትር ኢየሱስ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ይመሰክራል፡፡ሉቃ 1፡32፤ራእ 22፡16 የእሴይ በትር ማርያም ሳትሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

**ጥያቄ 4፦-** ያዕቆብ በሕልም ያየው መሰላል ማርያም ከሆነች ወደ እግዚአብሔር ማድረስ(መማለድ) ትችላለች፡፡ታዲያ ማርያም አማላጅ ሆና እንደት አትማልድም ትላላችሁ?

**መልስ፦-**

የኦርቶዶክሳውያን ቤተ እምነት ተከታዮችና መምህራን ያዕቆብ በዛ ምሽት ያየት መሰላል እግዚአብሔር ከላይ ሆኖ መላእክት በመሰላሉ ስወጡና ስወርዱ ያዬ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ይላሉ፤እነርሱ እንደ ብሉም መጽሐፍ ቅዱስ ግንሀሳባቸውን ፉርሽ ያደርጋል፡፡በመጀመርያ ስለ መሰላል ምንነት ታርካዊ ዳራ እንመለከት፦- መሰላል መውጫ ያለው አሁን የሚናውቀው ዐይነት መሰላል ሳይሆን በጥንት መሰጼጦምያ የሚገኙ ዚጉራት ያላቸው አይነት አለው፡፡ ይሄ መሰላል ከባቢሎን ግንብ አሰራር ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የመሰጼጦምያ ዚጉራቶች ምድርን ከሰማይ የሚያገናኙ ደረጃ ያላቸው በመሆኑ ሰማይና ምድርን ለማያያዝ የሰሩ ቤት ነው፡፡

ግንቡ ዚጉራት በመባል የሚታወቀው የመሰጴጦምያን ቤተመቅደስ መሠረቱ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ጎንና ጎኖቹ ሾጠጥ ብለው የሚወጡና ከላይ በኩል የሚጋጠሙ ናቸው፡፡እግዚአብሔር ከጫፍ ላይ ቆሞ የሚለው ቃል ይህንን ሀሳብ ይደግፋል፡፡በመሰጴጦምያ የሚገኙ ዚጉራት ለአምልኮ የሚወጡ ሰዎች ወደ አማልክታቸው የሚጸልዩበት ትንሽ ክፍል ከጫፍ ላይ አላቸው፡፡በዚህዉ ላይ የእግዚአብሔር ቤት...የሰማይ ደጅ ነው የሚሉት ሐረጋት ያዕቆብ ያየት መሰላል ከመሰጴጦምያ ዚጉራት ጋር የሚዛመድ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ዘፍ 11፡9

ታርካዊ ዳራ በአጭሩ ካየን አሁን ደግሞ ያዕቆብ ያየት መስላል ማርያም ያለመሆና ከመጽሀፍ ቅዱስ እንቃኝ ፡-

ያዕቆብ በሕልሙ ያየት መስላል ኢየሱስ መሆኑን ኢየስስ ራሱ ተናግሯል ፡፡ ሰማይ ስከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ አለ ዮሐ 1፡51 ኢየሱስ ራሱ መስላሉ እኔ ነኝ እያለ የኦርቶዶክሳውያን ቤተ እምነት ተከታዮችና መምህራን ማርያም ናት ማለታቸው ዮሐ 1፡51 ሳያነቡ የቀሩ ይመስላሉ፡፡የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ ያዕቆብ በሕልም እንዳየው ማለት ነው (ዘፍ 28፡8-12) ይህም ቤዛነት ወደ ዓለም የመጣው በእግዚአብሔር በተመረጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት መሆኑን ያሳያል ፡፡ ኢየሱስ ለደቀ

መዛሙርቱ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ ያለው ራሱ በሰማይና በምድር መካከል ያለ ድልድይ(መስላል) መሆኑን ስገልጽ ነው፡፡የመስጰጥምያ ዚጉራት በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች ወደ ሰማይ የሚያደርሰው መስላል(ግንብ) እንደሰሩ ፤ኢየሱስ በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች ወደ ሰማይ(እግዚአብሔር አብ) የሚያደርስ ሪሱ ብቻ መሆኑን አሳየ፡፡ለዚህም እኔ መንገድ፡እውነትና ሕይወት ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ማለቱ ወደ አብ የሚያደርስ መስላል(መንገድ) ከእርሱ በቀር ማንም እንደለለ ተናገረ፡፡ ሐዋ 4፡12፤ዮሐ 14፡6 እንዲሁም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ መካከለኛ እንደሆነ ሐዋርያዊ ጳውሎስም ተናግሯል፡፡1ጢሞ 2፡5 በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት መስላል ማርያም ሳትሆን ኢየሱስ እንደሆነ በግልጽ አስፍሮአል፡፡የኦርቶዶክሳውያን ቤተ እምነት ተከታዮችና መምህራን ሌላ መስላልና መንገድ ያስፈልገናል እያሉ መርከብ ያለመር እንደሚጠፋ በእውሸት እየፋነኑ የዋህ ሕዝብን ወደ ሲኦል እየነዱ ይገኛሉ፡፡

## ጥያቄ 4፡- "አምላክ ለማን ይማልዳል?"

ለሚለው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ:-ይህ ጥያቄ ብዙ ጊዜ የሚነሳው "መለኮት ከመለኮት ጋር ይነጋገራልን?" በሚል ጥርጣሬ ነው። መልሱ ግን ያለው በክርስቶስ "ሰው መሆን" (Incarnation) ምስጢር ውስጥ ነው።

በሰውነቱ ባህርይ ይህንን ተግባር ይፈጽማል ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው። እንደ አምላክነቱ ሰጪና ፈራጅ ሲሆን፣ እንደ ሰውነቱ (እንደ ሊቀ ካህንነቱ) ደግሞ ተቀባይና አማላጅ ነው።

ለማን ይማልዳል? ክርስቶስ የሚማልደው ለአብ ነው። ይህ ማለት ግን አብ ራርቶ ክርስቶስ ደግሞ አስታራቂ ነው ማለት አይደለም። ይልቁንም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ባቀዱት የድኅነት ምስጢር መሠረት፣ ወልድ ሰው ሆኖ

የሰውን ወገን ወክሎ በአብ ፊት መቆሙን ያሳያል። የቃል ኪዳን መካከለኛ: በአሮጌው ኪዳን ካህናቱ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ይቆሙ ነበር። በአዲሱ ኪዳን ክርስቶስ ራሱ "ሰው" በመሆኑ፣ የሰውን ጸሎትና ሕይወት ወደ መለኮት የሚያደርስ መሰላል ሆኗል።

2. የዕብራውያን መልእክት ቁልፍ ጥቅሶችና ትርጓሜያቸው

ይህ መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ሊቀ ካህንነትና አማላጅነት የሚናገር "የአማላጅነት መዝገበ ቃላት" ነው። በመጽሐፍህ ውስጥ በሚከተለው መልኩ ማስቀመጥ እንችላለን:-

ዕብ. 7:25 "ስለ እነርሱ ሊያማልድ ሁልጊዜ በሕይወት ይኖራልና" - አማላጅነቱ ለተወሰነ ጊዜ ሳይሆን እስከ ዓለም ፍጻሜ (እስከ ፍርድ) እንደሚቀጥል ያረጋግጣል።

ዕብ. 9:24"አሁን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ ይታይ ዘንድ..." - አማላጅነቱ በንግግር ብቻ ሳይሆን፣ በሕያው አካሉ (በቆሰለው ሥጋው) በአብ ፊት መታየት መሆኑን ያሳያል።

ዕብ. 4:15"ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ሊቀ ካህን አለን" - ክርስቶስ የሰውን ድካም ስለሚያውቅ የሚማልድልን በርኅራኄነትና በእውቀት መሆኑን ያሳያል።

ዕብ. 8:1-2"በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ ተቀመጠ... እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ [Liturgist/Priest] ነው" - በዙፋን መቀመጡ (አምላክነቱ) ከአገልጋይነቱ (ሊቀ ካህንነቱ) ጋር እንደማይጋጭ ያሳያል።

መለኮት (አብ): በበላይነት። ክርስቶስ (መካከለኛ): በአንድ እጁ መለኮትን (አምላክነቱን)፣ በሌላ እጁ ሰውን (ሰውነቱን) የያዘ። የአማላጅነት መስመር: ከሰው ወደ አብ በክርስቶስ በኩል የሚሄድ። የክርስቶስ አማላጅነት ግን "በገዛ ደሙ መቅረብ" (Presentation of His Sacrifice) ነው። ክርስቶስ የሚማልደው ተንበርክኮ ሳይሆን፣ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ቤዛነት በአብ ፊት "እንደ ታረደ በግ" ሆኖ በማሳየት እንደሆነ (ራእይ 5፡6) መግለጽ።

"ኢየሱስ አማላጅ ነው" ማለት "አምላክ አይደለም" ማለት አይደለም ይልቁንም አማላጅነቱ የአምላክነቱ መገለጫ የሆነው የፍቅሩ ማሳያ ነው ።

**ጥያቄ 5፡-** "መጽሐፍ ቅዱስ 'ለፍርድ ይመጣል' ይላል እንጂ 'ለአማላጅነት ይመጣል' አይልም፤ ታዲያ እንዴት አማላጅ ይባላል?"

**ምላሽ፡-** አዎ፣ ለፍርድ የሚመጣው በዳግም ምጽአቱ ነው፤ አማላጅነቱ (መካከለኛነቱ) ግን "አሁን" በሰማይ እያከናወነ ያለ ተግባር ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ፡- ዕብራውያን 7፡25 "ስለ እነርሱ ሊያማልድ ሁልጊዜ በሕይወት ይኖራልና" ይላል። ክርስቶስ ሁለት የሥራ ድርሻዎች አሉት። አሁን ባለንበት የጸጋ ዘመን "ሊቀ ካህንና አማላጅ" ነው፤

በዓለም መጨረሻ ግን "ጻድቅ ፈራጅ" ሆኖ ይመጣል። ዛሬ በአማላጅነቱ ተጠቅመን ንስሐ ካልገባን፣ ነገ በፈራጅነቱ ፊት መቆም አንችልም።

**ጥያቄ 6፡-** "ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ" የሚለው የመላእክትን አማላጅነት አይገልጽም?

**ምላሽ፡-**

አቀራረብ እንጂ አማላጅነት አይደለም፡- እዚህ ጋር መልአኩ የተሰጠው ተግባር ጸሎቱን "ማቅረብ" (Presenting) እንጂ "ማማለድ" (Mediating) አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ መላእክት "አገልጋይ መናፍስት" ናቸው (ዕብ 1:14)። ጸሎቱን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደሚያደርስ መልእክተኛ (Messenger) እንጂ፣ ጸሎቱ እንዲሰማ የራሳቸውን ጽድቅ ወይም ደም የሚጨምሩ "መካከለኛ" አይደሉም። ዕጣኑ የማን ነው? ብዙ የነገረ መለኮት ምሁራን እንደሚስማሙት፣ በቅዱሳን ጸሎት ላይ የሚጨመረው "ዕጣን" የክርስቶስ የማዳን ሥራና ጽድቅ ነው። ያለ ክርስቶስ ጽድቅ (ዕጣን) የቅዱሳንም ቢሆን ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መዓዛ አይኖረውም። ስለዚህ እዚህም ቢሆን መካከለኛ ክርስቶስ ነው። መልአኩ እዚህ ጋር "ሊቀ ካህን" ሳይሆን "አገልጋይ" (Waiter) ነው። ጸሎቱን ተቀብሎ በንጉሡ ፊት እንደሚያቀርብ አገልጋይ ይቆጠራል።

**ጥያቄ 7፡- የዘካርያስ መጽሐፍ (ዘካርያስ 1:12) - የመልአኩ ልመና**

"የእግዚአብሔርም መልአክ መልሶ፡- አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ... እስከ መቼ አትምራቸውም? አለ" የሚለው መልአኩ ስለ ሕዝቡ መለመኑን (ማማለዱን) አያሳይም?

**ምላሽ፡-**

መልአኩ ለራሱም ጥያቄ ነበረው፡- መልአኩ "እስከ መቼ?" ብሎ መጠየቁ የእግዚአብሔርን ምስጢርና ጊዜ እንደማያውቅ ያሳያል። ሁሉን የማያውቅ (Limited knowledge ያለው) ፍጡር ደግሞ የሁሉንም ሰው ጸሎት ሰምቶ ሊያማልድ አይችልም። መላእክትና ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙና ለቅዱሳን የሚያገለግሉ "ረዳቶች"

ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ብቸኛው "መንገድ" እና "መካከለኛ" ነው። ወደ ንጉሡ ለመድረስ በአገልጋዮቹ (በመላእክት) በኩል መዞር አያስፈልግም፤ ምክንያቱም ልጁ (ክርስቶስ) በሩን ከፍቶልናል (ዕብ 10:19-20)።

**ጥያቄ 8:-** ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም። ማቴዎስ 10፥41-42 በቅዱሳን ስም ቢናገለግል የእነርሱ ዋጋ አንቀበልም ወይ? ታዲያ አማላጅ ለምን አይባሉም ?

ነቢይ የነቢይ ዋጋ የሚለው አማላጅነትን እንደማያመለክት ተንትን ማቴዎስ 10፡41 ላይ የሚገኘው “ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል” የሚለው ቃል፣ ከቅዱሳን ምልጃ ጋር ሳይሆን ከሰውየው እምነት፣ ተሳትፎና በረከት ጋር የተያያዘ መሆኑን በሚከተሉት ነጥቦች መተንተን ይቻላል፦፡ ተቀባይነት እንጂ ልመና አይደለም ይህ ጥቅስ የሚያወራው ስለ መቀበል (**Hospitality/Reception**) እንጂ ስለ ልመና (**Intercession**) አይደለም። "መቀበል" ማለት አንድን ሰው በእምነት ማስተናገድ፣ መልእክቱን አምኖ መቀበልና ለአገልግሎቱ ድጋፍ መስጠት ማለት ነው። አማላጅነት ግን በአጥፊና በፈራጅ መካከል ቆሞ ስለ ሌላው ይቅርታን ወይም ምሕረትን መለመን ነው። ስለዚህ ጥቅሱ የሚናገረው ነቢዩን ስለሚቀበሉ ሰዎች እንጂ፣ ነቢዩ ስለ እነርሱ ስለሚያደርገው ልመና አይደለም።በሌላ በኩል."የነቢይ ዋጋ" የሚለው ትርጉም እዚህ ጋር "ዋጋ" የተባለው ነቢዩ ስለ አገልግሎቱ ከእግዚአብሔር የሚያገኘው መንፈሳዊ በረከት ወይም ክብር ነው። አንድ ሰው ነቢዩን በነቢይነቱ አምኖ ሲቀበለው፣ በነቢዩ አገልግሎት ውስጥ ተባባሪ (Partner) ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ መርህ መሠረት፣ በጦር ሜዳ የሚዋጋውና ዕቃ የሚጠብቀው እኩል እንደሚካፈሉ (1 ሳሙ. 30፡24)፣ ነቢዩን የሚረዳውም ሰው ነቢዩ ከሚሰበክው ቃልና ከሚሰራው ስራ የተነሳ የሚገኘውን በረከት አብሮ ይካፈላል ማለት ነው። ይህ "ሽልማትን መጋራት" እንጂ "በሰው በኩል መለመን" ማለት አይደለም። ጥቅሱ "ነቢዩ ያማልዳል" አይልም። ይልቁንም ተቀባዩ ሰው ነቢዩን ሲቀበል ያለው "አመለካከት" ወይም "እምነት" ምን መሆን እንዳለበት ያስረዳል። ሰውየው ነቢዩን የተቀበለው እንደ ተራ እንግዳ ሳይሆን "የእግዚአብሔር ሰው ነው" ብሎ ካመነ፣ እምነቱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ ያስጠዋል። ይህ የሚያሳየው የተቀባዩን ሰው መንፈሳዊ ብስለትና ለእግዚአብሔር ቃል ያለውን ክብር እንጂ፣ ነቢዩ በሰውየውና በእግዚአብሔር መካከል አማላጅ ሆኖ መቆሙን አይገልጽም። በዚሁ ምዕራፍ (ማቴ. 10) ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለስብከት ሲልካቸው የሰጠው መመሪያ ነው። ደቀ መዛሙርቱ ሲሄዱ የሚቀበላቸው ሰው በረከት እንደሚያገኝ፣ የማይቀበላቸው ግን ፍርድ እንደሚሆንበት ይናገራል። ስለዚህ "የነቢይ ዋጋ" ማለት ወንጌልንና የወንጌል መልእክተኞችን የመቀበል በረከት እንጂ፣ ነቢዩ ለሰዎች ይቅርታን የሚያስገኝ አማላጅ ነው ማለት አይደለም። በአጭሩ "ነቢይን በነቢይ ስም መቀበል" የሚለው ኃይለ ቃል የሚያሳየው መንፈሳዊ ተሳትፎን (Spiritual Partnership) ነው። አንድ ሰው ለአንድ አገልግሎት ድጋፍ ሲያደርግና አገልግሎቱን ሲቀበል፣ በዚያ አገልግሎት ውስጥ እንዳለ ተቆጥሮ የዚያን አገልግሎት በረከት ይካፈላል። ይህ ደግሞ ከአማላጅነት (ከመካከለኛነት) ተግባር ጋር ፈጽሞ የተለየ ጽንሰ-ሐሳብ ነው።

## ማጠቃለያ (Conclusion)

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በዝርዝር ለመመልከት እንደሞከርነው፣ የክርስቶስ "አማላጅነት" እና "ፈራጅነት" እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሳይሆኑ፣ በአንድ አካል ላይ የሚገለጡ የአምላካችን የፍቅርና የጽድቅ ስራዎች ናቸው። ክርስቶስን አማላጅ (መካከለኛ) ስንለው፣ እርሱ የሰውን ልጅ ከአምላክ ጋር ያስታረቀበትን የቤዛነት ስራውንና አሁንም በአብ ፊት እኛን ወክሎ ያለውን ሊቀ ካህንነት ማለታችን ነው። "ፈራጅ" ስንለው ደግሞ፣ የምሕረትና የጸጋው ዘመን ሲያበቃ በሠራነው ሥራ ሁሉ ሊፈርድብን በግርማ የሚመጣው የጽድቅ ዳኛ መሆኑን ማወጃችን ነው።

አንባቢ ሆይ! ዛሬ ያለንበት ዘመን የጸጋ ዘመን ነው። ክርስቶስ በሰማያዊ መቅደስ ሊቀ ካህናችንና አማላጃችን ሆኖ እጁን ዘርግቶ ይጠብቀናል። ዛሬ በእርሱ አማላጅነት (መካከለኛነት) ተጠቅመን ከእግዚአብሔር ጋር ካልታረቅን፣ ነገ በፈራጅነቱ ፊት መቆም ይከብደናል። ስለዚህም ነው ቅዱስ ቃሉ "ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታደንድኑ" የሚለን (ዕብ. 4፡7)።

ይህ መጽሐፍ በልባችሁ ውስጥ ለውጥን እንዲያመጣ፣ ስለ ክርስቶስ ያላችሁን እውቀት እንዲያሳድግና ለቤተክርስቲያን አንድነት መሠረት እንዲሆን ጸሎቴ ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ያለውን ሰላምና ጸጋ አብዝቶ ይስጣችሁ።

## ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography)


1. አዲሱ መደበኛ ትርጉም (NIV)

2. የአዲስ ኪዳን ማብራርያ

3. የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓገም ስልት (Hermenutics) በኢትዮጵያ በሙሉ ወንጌል ሥነ-መለኮት ሴምናር የተዘጋጀ

4. እንዴ መለከ ጼዴቅ (በዶ/ር መልሳቸው መስፍን)

5. የትምህርቴ ሥላሴ መሠረታዊያን (ዶ/ር ተስፋዬ ሮቤሌ)

6. የዕብራውያን መጽሐፍ ማብራርያ (SIM)

7. ደብተራ ኦርት (BY GBV)

8. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት

9. የአዲስ ኪዳን መካከለኛ (ከሀይማኖት አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ)

10. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ምግባር (በሮበትርትስ መኩርያ)

11. የቤተክርስትያን ታርክ (በስሜ ታደሰ 2002 ዓ.ም)

12. ትምህርተ-እግዚአብሔር (ቄስ ኮለነ ማንስል)

13.የመናፍቂያን ጥያቄ (በማህበረ-ቅዱሳን የተዘጋጀ)

14. ትምህርተ ተዋህዶ (በማህበረ-ቅዱሳን የተዘጋጀ)

15. ዓምደ ሃይማኖት (በካቶሊክ የቤቴክርስትያ የተዘጋጀ)

16. መንጦላዕት (ያልተጋረዱ መጋረጃዎች) መ/ር ገነኔ ጣሳው ገ/ማርያም

17. Christology in Ethiopian perspective

18. Christology (Ethiopia full gospel church)



*አገልጋይ ኢያሴው ዋቀዮ(መ/ር) ጌታን ከተቀበለ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ በትጋት የሚያገለግል እና እውነት ላልደረሳቸው እየመሰከረ መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት የሚያነቢ የስነ-መለኮት አንባቢ እና መጽሐፍ ወዳድ ትጉህ አገልጋይ ነው ። ብዙ ትምህርቶችን በተለያዩ ቤተክርስቲያን እያስተማረ የሚገኝና በተለይ በሀገራችን የሰባልያን መንፈሳዊ ልጆች የሆኑ በተለምዶ ኦንል ጅሰስ የሚባሉ መናፍቃዊ ድርጅት ላይ ሂስ በመሰንዘር በትጋት የሚያገለግል ነው ። ወንድማችን ብዙ መጽሐፍ ያዘጋጀ ሲሆን ከገንዘብ እጥረት ምክንያት ሳይታተሙ እስከ አሁን ያሉ አሉ። እግዚአብሔር ዘመኑን ይባርከው።*

**አለማዮሁ ወ/ዮሐንስ (ፓ/ር)**

**ለመጽሐፍ ሕትመት ድጋፍ ከፈለጉ**

**CBE 1000295626295**

**Telebirr 0953755701**

# 2018

# መ/ር አያሌው ዋቀዮ